ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቅጽ 02 ቁ. 015
ሚያዚያ 2018 ዓ.ም እንደራሴ



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ - ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው :: ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው ::

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፡- ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።
- አዲስነት፡- ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፡- ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

BRIDGE Research & Innovation - Parliaments. Peace. Policy


+251 99 808 5013

+251 115 57 74 96

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

UNECA, SA Building, 9th Floor,

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

## ማውጫ


የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ሚያዚያ ክራሞት ........ 2
በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች ........ 2
1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ........ 4
1.1 የጸደቁ ሕግጋት ........ 4
1.2 ረቂቅ ሕግጋት ........ 5
1.3 አሥረጂ መድረኮች ........ 7
2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........ 10
2.1 የተቋማት ሪፖርቶች ........ 10
2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ........ 26
3. የፓርላማው ዲኘሎማሲ ........ 33
4. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው ........ 38
5. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች? ........ 40
6. ሹመቶች ........ 42
7. የብሪፎ ደሰሳዊ ምልከታ፦ በሲቪል ማኅበረሰቡ ከየት ወዴትነት እና ቀጣይ ዕድሎች ........ 43
7.1. ሲቪል ማኅበረሰብ ሲሉ... ........ 43
7.2. የአጼው ዘመነ-መንግሥት ........ 44
7.3. ጸረ-ሲቪል ማኅበረሰቡ ደርግ ........ 45
7.4. የኢሕአዴግ ሦሥቱ ምዕራፎች ........ 47
7.5. የባለሥልጣኑ መቋቋም ........ 49
7.6. ተስፋው በኗልን? ........ 50
7.7. ከተቋሙ ሪፖርቶች ጥቂት ነጥቦች ........ 51
7.8. ምርጫ 2018 እና የሲቪል ማኅበረሰቡ ሚና ........ 53
7.9. የብሪፎ ምክረ-ሐሳቦች ........ 55

**ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቅጽ 2 ቁ.15/ሚያዚያ 2018 ዓ.ም.**

## የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ሚያዚያ ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሚያዚያ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን አከናውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋትን ማጽደቅ፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን መከወን እና የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶችን ማድረግ የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖች ነበሩ። ይኽች የእንደራሴ ዐሥራ አምስተኛ ዕትምም፣ እኒኽን ጉዳዮች በመልክ በመልካቸው አጠናቅራ እና ለወሩም እንዲሆን አንድ የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታን አካታ እንዲኽ ተጠናቅራለች።

## በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳዎች |
|---|---|---|
| 15ኛ መደበኛ ስብሰባ | ሚያዚያ 13 | * የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩየሪቲ ዐዋጅን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ማጽደቅ፤<br>* የስፖርት ልማት እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ማጽደቅ፤ |
| 16ኛ መደበኛ ስብሰባ | ሚያዚያ 15 | * የተጓደሉ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አመራሮችን ሹመት መርምሮ ማጽደቅ<br>* የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ማድመጥ፤ |

| | | |
|---|---|---|
| 17ኛ መደበኛ ስብሰባ | ሚያዝያ 20 | * በኢፌዴሪ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገ የብድር ስምምነትን ማጽደቅ፤<br>* በኢፌዴሪ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ማኅበር መካከል የተደረገ የብድር ስምምነትን ማጽደቅ፤<br>* የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ሠላማዊት ካሳ በምክር ቤቱ ተገኝተው ከእንደራሴዎቹ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የሚሰጡትን ምላሽ ማድመጥ፤<br>* የሳይበር ደኅንነት ረቂቅ ዐዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤ |
| 18ኛ መደበኛ ስብሰባ | ሚያዚያ 22 | * በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ፤ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በአንጎላ ሪፐብሊክ፤ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በባንግላዲሽ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ እንዲኹም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በኢስዋቲኒ ንጉሠ ነገሥት መንግስታት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የቀረቡ አራት ረቂቅ ዐዋጆችን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤<br>* በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤<br>* በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤<br>* የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ አባላትን ሹመት መርምሮ ማጽደቅ፤ |
| 19ኛ መደበኛ ስብሰባ | ሚያዝያ 28 | * የውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴርን የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ<br>አፈጻጸም ማድመጥ፤ |

## 1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሚያዚያ **ኹለት ዐዋጆችን** ሲያጸድቅ፣ የኢፌድሪ መንግስት ከተለያዩ መንግስታት ጋር **የተደረጉ ረቂቅ ስምምነቶችንም**፣ ይመለከታቸዋል ወዳላቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል። ከዚያ ባለፈም፣ ሦሥት የአሥረጂ መድረኮችንም ከውኗል።

### 1.1 የጸደቁ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ሚያዚያ ካካሄዳቸው መደበኛ ስብሰባዎች መካከል፣ በ15ኛ መደበኛ ስብሰባው ኹለት ረቂቅ ዐዋጆችን አጽድቋል። ቀዳሚው ዐዋጅ የነበረው፣ **የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ ዐዋጅ**ን ለማሻሻል የቀረበው ረቂቅ ሲሆን፤ ረቂቁን አሥመልክቶ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ ነበሩ።

የማሻሻያ ዐዋጁ በሚዘረጋቸው አሠራሮች እና ቴክኖሎጂዎች መሠረት ያሉትን የደኅንነት ስጋቶች የሚፈታ ስለመሆኑ የተናገሩት የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ፣ በዓለም ዓቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ስታንዳርድ እና መለኪያ መሠረት የተሻለ የአቪዬሽን ሴኩዩሪቲ መገንባት የሚያስችል እንደሆነ አሥረድተዋል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ ቁጥር 1412/2018 አድርጎ በ2 ተቃውሞ እና በ2ድምፅ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።



*የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ በረቂቅ ዐዋጁ ንባብ ወቅት፤*

እንደራሴዎቹ በዚኹ የወሩ 15ኛው መደበኛ ስብሰባቸው ያጸደቁት ኹለተኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አሥተዳደርን** የተመለከተው ነበር። የዚኽን ረቂቅ ዐዋጅ ሪፖርት እና ውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወርቀ ሰሙ ማሞ ነበሩ።

ረቂቅ ዐዋጁ፣ በስፖርቱ ዘርፍ አካታች፣ አሳታፊ፣ ዘመናዊ እና አሥተዳደራዊ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ምቹ መደላድል ይፈጥራል ያሉት ሰብሳቢዋ፣ በዘርፉ የሚታዩ የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን የሚፈታ፣ የስፖርት መሠረተ ልማትን እና ማሠልጠኛ ተቋማትን

በመገንባት እንዲኹም የስፖርት ግብዓት አምራቾችን እንደሚያበረታታ ተናግረዋል ተብሏል። የዐዋጁን አሥፈላጊት በሚመለከት አሥተያየት ከማቅረብ ባለፈ፣ አፈጻጸም ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ላሏቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ተጨማሪ ማብራሪያ የሰጡት፣ የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ እንደነበሩ ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ሚኒስትሯም፣ ስፖርት የኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ እንዲሆን ዘርፉን የያዙትን ማነቆዎች በአሰራር እና ሥርዓት መፍታት ያስፈልጋል ሲሉ የዐዋጁን አሥፈላጊነት ጠቁመዋል። በመጨረሻም እንደራሴዎቹ የቀረበላቸውን ረቂቅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1413/2018 አድርገው በሙሉ ድምጽ ይጸድቅ ዘንድ ፈቃዳቸው ሆኗል።



***የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወርቀ ሰሙ ማሞ፣ የረቂቅ ዐዋጁን ምክረ-ሐሳብ ሲያቀርቡ፤***

## 1.2 ረቂቅ ሕግጋት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በ18ኛው መደበኛ ስብሰባቸው ይመለከታቸዋል ወደሏቸው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ከመሯቸው ረቂቅ ዐዋጆች መካከል አንዱ፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት** ነበር።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ ሻንቆም፣ ስምምነቱ በአገራቱ መካከል የጋራ ሳይንሳዊ እና ጥናታዊ የምርምር ሥራዎችን ለማጠናከር እና ለማሳደግ እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር መሠረተ-ልማት ግንባታ እንዲኹም የምርምር ውጤትን ወደ ገበያ የማቅረብ ተቋማዊ ቅርጽ በማስያዝ የኹለቱ አገራት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንደሚያስችል የጠቀሱት የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ፣ የሀገር በቀል የምጣኔ ሀብት ዕድገትን ለማፋጠን የዓሳ ሀብት ልማት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው እንደመሆኑ ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ወደ ውጭ ኤክስፓርት ለማድረግ ሩሲያ በዘርፉ ካላት ከፍተኛ ልምድ ለማካበት እንደሚያግዝም አስገንዝበዋል ተብሏል። ምክር ቤቱም፣ ረቂቅ ዐዋጁን፣ ዐዋጅ ቁጥር 17 /2018 አድርጎ ለውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መርቶታል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኹ መደበኛ ስብሰባቸው የተመለከቱት ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በተለያዩ አገራት መካከል የተደረጉ የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጆች**ን እንደነበር ተዘግቧል። በ'ነዚኽ ረቂቆች ዙሪያም የተናገሩት፣ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ፣ ረቂቅ ዐዋጆቹ ለኢትዮጵያ የአየር ትራንስፖርት እና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ያላቸውን ጉልህ ሚና ለእንደራሴዎቹ አቅርበዋል።

በቅድሚያ ያቀረቡትም **በኢትዮጵያ መንግስት እና እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ** መካከል እንዲፈረም የቀረበውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ሲሆን፤ ስምምነቱ ለአየር መንገዶች ወደ ተመረጡ መዳረሻዎች በቀጥታ ለማረፍ እና ምቹ የአቪዬሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ከማስቻል በተጨማሪ አገራቱ የአቪዬሽን እና የበረራ ቁሳቁሶችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንዲችሉ እድል የሚፈጥር መሆኑንም ገልፀዋል ተብሏል።

በመቀጠልም፣ **በአንጎላ ሪፐብሊክ እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል** የአየር አገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ ለምክር ቤቱ ያቀረቡት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ስምምነቱ በአገራቱ መካከል ያለውን ረዥም ዘመናት ያስቆጠረ ግንኙነት ለማሳደግ እና አገራቱ በዘርፉ ያገኙትን ትርፍ ያለምንም ገደብ ወደ አገራቸው ለማስገባት ዕድል የሚፈጥር መሆኑንም ሲናገሩ ተደምጠዋል።

**በኢትዮጵያ መንግሥት እና በባንግላዲሽ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መካከልም** ስምምነት እንዲደረስበት የቀረበውን የአየር አገልግሎት ረቂቅ ስምምነትም ለእንደራሴዎቹ ያቀረቡት የመንግስት ተጠሪው፣ የስምምነቱ ረቂቅ በአገራቱ መካከል እያደገ የመጣውን የአየር ትራንስፖርት ፍሰት ከግምት ያስገባ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል።

ሌላይኛው፣ **በኢትዮጵያ እና በኢስዋቲኒ ንጉሠ ነገሥት መንግሥታት መካከል** የተደረገ የአየር አገልግሎት ረቂቅ ስምምነት ሲሆን፣ ያለ በረራ ድግምግሞሽ ገደብ የጭነት በረራዎችን ማከናወን ጨምሮ ለበረራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባትን የሚያካትት በመሆኑ፣ የስምምነቱ ረቂቅ የበረራ ወጪን እንደሚቀንስ የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። በአገራቱ መካከል የተደረጉትን የአየር አገልግሎት ረቂቅ ስምምነቶችን በሙሉ ድምፅ ለውጪ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ መርቷል።



*በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ ሻንቆ፣ የስምምነቶቹን ረቂቆች ሲያቀርቡ፤*

## 1.3 አሥረጂ መድረኮች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ሚያዚያ ወር፣ **ሦሥት የአሥረጂ መድረኮችን** አካሂደዋል።

በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው የአሥረጂ መድረክ፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የጉምሩክ ዐዋጅ ቁጥር 859/2006ን ለኹለተኛ ጊዜ እንደገና ለማሻሻል** በቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ ላይ ያካሄደው እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄም፣ ረቂቅ ዐዋጁ ከዐብይ ኢኮኖሚው ማሻሻያ እንዲኹም ከዓለም ዓቀፋዊ እና አህጉራዊ ድንጋጌዎች ጋር የተናበበ ለማድረግ እና የጉምሩክን አሰራር ለማዘመን የተደረገ ማሻሻያ መሆኑን በአሥረጂ መድረኩ ላይ ተናግረዋል ተብሏል።

የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ፣ ኮንትሮባንድ የጫኑ ተሽከርካሪዎች መውረስን በተመለከተ የተሽከርካሪው ባለቤት እውቅና የሌለው መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድቶ ምላሽ የማያገኝ ከሆነ እስከ ፍርድ ቤት ድረስ ይግባኝ የማለት መብቱ የተጠበቀ መሆኑንም ሰብሳቢው አስገንዝበዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለማየሁ፣ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ የገቢ እና ወጭ ንግድን ከማሳለጥ እንዲኹም ከዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ጋር የተናበበ ከማድረግ ባሻገር፣ የአገርን ሉዓላዊነት በማስከበር ረገድ አይነተኛ ሚና እንደሚኖረውም ገልፀዋል ተብሏል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አዘዘው ጫኔ በበኩላቸው፣ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ በሕጋዊ መንገድ የሚሰሩ ነጋዴዎችን እና የትራንስፖርት ባለቤቶችን የሚያበረታታ እንጂ ስጋት ውስጥ የሚጥል እንዳይሆን፣ በሕዝባዊ የአሥረጂ መድረኩ የተነሱ ጉዳዮችን እንደግብዓት መውሰድ እንደሚገባም አመላክተዋል።

የፌደራል ፖሊሲ ምክትል ኮሚሽነር መላኩ ፈንታ በተራቸው፣ በኮንትሮባንድ ንግድ ከተወረሱ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ የተቋሙን አቅም ከመገንባት ባለፈ፣ በኮንትሮባንድ መከላከል ሥራ ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን ታሳቢ ማድረግ እንዳለበት ማንሳታቸውም ተጠቅሷል።

የገንዘብ ሚኒስቴር ከፍተኛ የሕግ ባለሙያው አብርሃም ረጋ በበኩላቸው፣ ዐዋጁን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት በሥራ ላይ ያለው የጉምሩክ ዐዋጅ ለበርካታ ዓመታት በማገልገሉ የዐዋጁን ድንጋጌዎች ዓለም ዓቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም፣ እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለመደገፍ፣ በቀጠናው ካለው የንግድ ስምምነት ጋር ለማጣጣም፣ ድንበርን ለመጠበቅ እንዲኹም ሕጋዊ ንግድን እና የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን ለማበረታታት ይቻል ዘንድ የተዘጋጀ ረቂቅ መሆኑን ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤*

እንደራሴዎቹ በወሩ ካካሄዱት የአሥረጂ መድረኮች መካከል ሌላይኛው፣ በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በመረጃ ነጻነት ዐዋጅ ዙሪያ** ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ያካሄደው ነበር። የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነም፣ በመረጃ ነጻነት ረቂቅ ዐዋጅ ግልጽ ያልሆኑ ሐሳቦች፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ የሚሰጥበት መሆኑን አመላክተው ውይይቱን በይፋ መጀመሩን ተናግረዋል።

ከዚያ ባለፈም፣ መረጃ ማግኘት የዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ቢሆንም መረጃ የወሰዱ አካላትም የወሰዱትን ትክክለኛ መረጃ ለሕዝብ በማድረስ ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባቸው ያነሱት ሰብሳቢው፣ በረቂቅ ዐዋጁ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሐረጋት እና ቃላት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ከሆነም፣ በውይይቱ በተጠቆመው መሠረት ረቂቅ ዐዋጁን እንደገና ማየት እንደሚያስፈልግም አሳስበዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንደሞ በበኩላቸው፣ ከምክር ቤት አባላት፣ ከቋሚ ኮሚቴው እና ከምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሕግ ክፍል የተነሱት ጥያቄዎች ረቂቅ ዐዋጁን ለማዳበር ጠቃሚ በመሆናቸው ረቂቁን ዳግም መፈተሽ እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂ ወይዘሮ ስመኝ ውቤም፣ የዐዋጁን አስፈላጊነት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግሥት እና በዓለም ዓቀፍ ድንጋጌዎች መሠረት መረጃን ሕዝቡ እንዲያገኝ ታስቦ የተዘጋጀ ረቂቅ ዐዋጅ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

ዕንባ ጠባቂዋ አክለውም፣ መረጃ ከሰጡ አካላት የተገኘው ትክክለኛ መረጃ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ረቂቅ ዐዋጁ ከመዘጋጀቱ በፊት ጥናት መደረጉን እና ከሌሎች አገራትም ልምድ መወሰዱን ለመድረኩ ተሳታፊዎች ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ በአሥረጂ መድረኩ ወቅት፤*

የወሩ ሦሥተኛው የአሥረጂ መድረክ የነበረው፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት፣ የቁልፍ መሠረተ ልማቶች **የሳይበር ደኅንነት ዐዋጅን አስመልክቶ** የተካሄደው እንደነበር መረጃው ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ረቂቅ ዐዋጁ ቁልፍ የመንግስትም ሆነ የግል መሠረተ ልማቶችን ከሳይበር ጥቃት መጠበቅ የሚያስችል መሣሪያ መሆኑን ገልፀው፣ ቋሚ ኮሚቴው ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ረቂቅ ዐዋጁን በጥልቀት መርምሮ የውሳኔ ሐሳብ እንደሚያዘጋጅ ጠቁመዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ ዓለም ውስብስብ እና ተለዋዋጭ በሆነ የቴክኖሎጂ ለውጥ ውስጥ ባለችበት በዚኽ ወቅት፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከፍተኛ የሳይበር ጥቃቶች እንደሚፈፀሙ ገልፀው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን ከእነዚኽ ጥቃቶች በመጠበቅ የአገርን ሉዓላዊነት በማረጋገጥ ረገድ አይነተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው አመላክተዋል ተብሏል።

ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ ከፈንድ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ ከግለሰብ የሚሰበሰብበት አግባብ አለመኖሩን በዐዋጁ በግልፅ ማመላከት እንደሚገባ ጠቁመው፣ ከቅጣት አጣጣል ጋር ያለውን ፍትሓዊነት፣ ከአገራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ሕግጋት ጋር ያለውን ተናባቢነት እንዲኹም ከሰብዓዊ መብት ጋር በተያያዘ ቋሚ ኮሚቴው በጥንቃቄ የሚያየው መሆኑን መናገራቸውን መረጃው ጠቁሟል።

በአሥረጂ መድረኩ ላይ የተገኙት የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተሯ ትዕግስት ሃሚድ በበኩላቸው፣ የሳይበር ጥቃቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን ጠቅሰው፣ የሳይበር ጥቃቶች በአገር ምጣኔ ሀብት እንዲኹም በዜጎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ፣ ረቂቅ ዐዋጁ እነዚኽን ጥቃቶች ለመመከት አስቻይ ኹኔታዎችን እንደሚፈጥር ተናግረዋል ተብሏል።

ዋና ዳይሬክተሯ አክለውም፣ የዐዋጁ መውጣት ለቁልፍ መሠረተ-ልማቶች ሕጋዊ ጥበቃ በማድረግ አገሪቱ በነጻ የንግድ ቀጠናው ላይ ያላትን ተወዳዳሪነት ከማሳደግ ባሻገር፣ የዲጂታል ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ ረገድ ጉልህ ፋይዳ እንደሚኖረውም አመላክተዋል።



*የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተሯ ትዕግስት ሃሚድ፣ ረቂቅ ዐዋጁን ሲያብራሩ፤*

## 2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ሚያዚያ ወር፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች **የሃያ የፌደራል ተቋማትን የበጀት ዓመቱን የዘጠኝ ወራት ሪፖርት** አድምጠዋል።

### 2.1 **የተቋማት ሪፖርቶች**

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በወርኃ ሚያዚያ ካደመጧቸው ተቋማት መካከል ቀዳሚው፣ **የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትሯን የቃል ሪፖርት** ነበር። ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 17ኛ መደበኛ ስብሰባው የቱሪዝም ሚኒስቴርን የሥራ አፈጻጸም ገምግሟል። በዚኽም የአገሪቱን የቱሪዝም ሀብቶች ከመጠበቅ እና ከማልማት አኳያ፣ በተለይም በሰው ሠራሽ እና በተፈጥሮ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ታሪካዊ ቅርሶች ከመጠገን እና ከመንከባከብ አንጻር ምን እየተሠራ እንደሆነ ለሚኒስትሯ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሣ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ሲሰጡ፣ የአገሪቱ ታሪካዊ ቅርሶች ለትውልድ እንዲተላለፉ አስፈላጊው ጥበቃ እና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን ገልጸዋል። ሚኒስትሯ አክለውም፣ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከማልማት አንጻር በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከ800 በላይ የቱሪዝም መስህቦች መመዝገባቸውን እና ከእነዚኽም መካከል 300 ያኽሉት በተመጣጣኝ ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልማት እንደሚችሉ በጥናት መለየቱን ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋቸዋል።



*የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሣ፣ በሪፖርቱ ወቅት፤*

በወርኃ ሚያዚያ፣ የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን በማቅረብ ኹለተኛው ተቋም **የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን** ነበር። የባለሥልጣኑን ሪፖርት ያደመጠው በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ በመድረኩም በሲቪል ማኅበራት አሠራር፣ የማኅበራት ምዝገባ ሒደት፣ በጎ ፈቃደኝነት፣ የማኅበራት ገንዘብ አጠቃቀም እና በምርጫ ዝግጅት ዙሪያ ያተኮረ ሪፖርት መቅረቡ ተዘግቧል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱ፣ በአገሪቱ የሚደራጁ የሲቪል ማኅበራት ከቁጥር ባለፈ በጥራት እና በይዘት ኢትዮጵያን የሚመጥኑ እንዲሆኑ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል።

እንዲኹም 7ኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሓዊ እና ተአማኒ እንዲሆን የሲቪል ማኅበራት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በምርጫ ዙሪያ የሚሰሩ ማኅበራትን አቅም የማብቃት ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና ማኅበራቱ በማንኛውም ወገን ተጽዕኖ ሥር ሳይወድቁ ገለልተኛ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግም አመላክተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፣ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ጥረት ከመንግስት የልማት ዕቅድ ጋር ተቀናጅቶ ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበዋል። ማኅበራቱ የሚሰሩት ሥራ ከአገሪቱ የልማት ግቦች ጋር የተቆራኘ እንዲሆን እና የሕዝብን ተጠቃሚነት እንዲያሰፋ፣ ባለሥልጣኑ በየደረጃው ያለውን የቁጥጥር እና የክትትል ሥራ በመስክ ምልከታ ጭምር ታግዞ ማከናወን እንዳለበትም ምክትል ሰብሳቢው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሳምሶን ቢራቱ በበኩላቸው፣ መጪው አገራዊ ምርጫ ዲሞክራሲያዊ፣ ፍትሓዊ እና ተአማኒ ሆኖ እንዲጠናቀቅ በምርጫ ዙሪያ የሚሰሩ ማኅበራት ሚና ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፤ በምርጫ ሂደት ላይ የሚሳተፉ የሲቪል ማኅበራት ያላቸውን ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት በመረዳት ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውጤታማ አሥተዋጽዖ እንዲያበረክቱ አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል ተብሏል፤ (በዚኽ የባለሥልጣኑ ሪፖርት መነሾ፣ እንደራሴ ያዘጋጀችውን ዳሰሳ በገጽ 44 ይመለከቷል)።



*የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት፣ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ሪፖርት ሲያደምጡ፤*

በዚኹ የሚያዚያ ወር፣ ሦሥተኛው ተረኛ የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የትምህርት ሚኒስቴር** ሲሆን፤ የሚኒስቴሩን ሪፖርት ያደመጠው እና መታየት አለባቸው የሚላቸውን ግምገማዊ አስተያየቶቹን የሰጠው በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮም፣ ቀደም ሲል በምክር ቤቱ የጸደቁ ሦሥት ዐዋጆች ወደ ሥራ የገቡበት ሁኔታ በጥንካሬ የሚነሳ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይም ዩኒቨርሲቲዎች ‘ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ራስ-ገዝነትን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ ትግበራ በበጎ ጎኑ የሚነሳ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ ባለፉት ዓመታት ጉልህ ለውጥ ከታየባቸው ዘርፎች መካከል የትምህርት ምዘና እና የፈተናዎች አገልግሎት ዘርፍ፣ እንዲኹም የአዳዲስ ሥርዓተ-ትምህርቶች ትግበራ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ማንሳታቸው ተጠቅሷል። ትምህርት ለትውልድ የተሰኘው

አገራዊ ንቅናቄን በተመለከተ ከቦታ ቦታ የሚታየው የአፈጻጸም ልዩነት ሊታረም እንደሚገባው ያነሱት ሰብሳቢው፣ የ2018 አገራዊ ፈተናን በተመለከተም ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ በማየት ቅድመ ዝግጅት ሊደረግ እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጠዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ ከፕሮፌሰርነት ማዕረግ ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር መፍታት እንደሚገባ፣ የማስተማሪያ ሆስፒታሎችን አቅም መገንባት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ለተሽከርካሪ ኪራይ የሚያወጡትን በጀት ወደ ግዢ ሊቀይሩ እንደሚገባ እና ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለተማሪዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባም ሰብሳቢው ጨምረው አስገንዝበዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው በበኩላቸው፣ የሥርዓት ትምህርት ፖሊሲ እና ዓላማው፣ ዘመኑን የዋጀ መሆን እንዳለበት እና ትምህርት የኹሉም ዘርፎች መሰረት በመሆኑ ለውጤታማነቱ አበክሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋም፣ ከመውጫ ፈተናዎች ጋር በተያያዘ የግል ዩኒቨርሲቲዎች አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመው፣ ቀደም ሲል ዩኒቨርሲቲዎቹ ለተማሪዎች ውጤት ማነስ የተማሪዎችን የመግቢያ ጥራት ምክንያት የነበረው ችግር አዲሱ የ12ኛ ክፍል የፈተና ስርዓት ከመጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የመውጫ ፈተና የሚሰጥበት በመሆኑ ትክክለኛውን ጥራት ያሳያል ብለዋል።



*የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በቴክኖሎጂ በመታገዝ በተሰራው ሥራ ውጤት እየተገኘበት መሆኑን ያነሱት ፕሮፌሰሩ፣ ከተማሪዎች የፈተና ኩረጃ ጋር በተያያዘ በተደራጀ መልኩ የሚደረጉ ሙከራዎች ቢኖሩም፣ እየተወሰደ ባለው ጥብቅ እርምጃ በእጅጉ እየቀነሰ መምጣቱን ገልጸው፣ ከትምህርት ስርቆት ጋር በሚተባበሩ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወሰድ ማስጠንቀቃቸው ተሰምቷል።

**የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣንም፤** በዚኹ ወር በዐራተኛነት የበጀት ዓመቱን የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸሙን፣ በምክር ቤቱ የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቦ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ኘ/ር መሃመድ አብደም፣ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለአገሪቱ የአቪየሽን ዘርፍ ዕድገት እና ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ስኬት የጀርባ አጥንት ሆኖ እያገለገለ የሚገኝ ተቋም ነው ቢሉም፣ ተቋሙ እያከናወነ ያለውን ሥራ ለሕዝብ

በማስተዋወቅ ረገድ ክፍተቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ተቋሙ በ2030 ሥራ ይጀምራል ተብሎ የሚጠበቀውን የቢሾፍቱ ዓለም ዓቀፍ አየር መንገድ ታሳቢ ያደረገ እና የአየር መንገዱን ተወዳዳሪነት ሊያስቀጥል የሚችል የቁጥጥር ሥርዓት እና ተቋማዊ ቁመና ሊገነባ እንደሚገባም ሰብሳቢው ጨምረው ተናግረዋል። የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዮሐንስ አበራ በበኩላቸው፣ ለደንበኞች የሚሰጠው አገልግሎት ይበልጥ ቀልጣፋ እና ተደራሽ እንዲሆን የዲጂታላይዜሽን ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን አንስተው፤ የሚመሩት ተቋም፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በአየር ክልል ደኅንነት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በገቢ አሰባሰብ ረገድ አበረታች ውጤቶች ማስመዝገቡን ተናግረዋል ተብሏል።



*የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ኾ/ር መሃመድ አብዶ፣ በሪፖርቱ ወቅት፤*

በዚኹ ሚያዚያ ወር፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በአምስተኛነት ሊያደመጥ የመረጠው የፌደራሉ ተቋም፣ **የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን** ሲሆን፤ ተቋሙም የዚኽኑ ዓመት የ9 ወራት አፈጻጸሙን ለኮሚቴው አባላት አቅርቧል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግሥቱ፣ ጊዜ ያለፈባቸው ውሳኔዎችን በሚመለከት ኅብረተሰቡ ላይ ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ ይኽን ለመቅረፍ ጠንክሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል ተብሏል። ተዘዋዋሪ እና ምድብ ችሎቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች መኖራቸውን ያነሱት ሰብሳቢዋ፣ ይኽንንም ችግር አሰራር ዘርግቶ ማሻሻል እንደሚገባ ተናግረዋል።

የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፣ መመሪያዎችን በማውጣት እና ሥራ ላይ በማዋል ረገድ እንዲኹም የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች አበረታች መሆናቸውን ገልፀዋል። ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ በፌዴራል ፍርድ ቤት እና በክልሎች መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር በአፈጻጸም ላይ የታዩ ልዩነቶችን ማጥበብ እንደሚያስፈልግም ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቅሳል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንቱ ቴዎድሮስ ምህረት በተራቸው፣ የዳኞችን ትጋት እና ውጤታማነትን በሚመለከት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፤ የሠራተኞች ማበረታቻ በውጤት ደረጃ ብቻ ማተኮር

ወደ ኋላ የሚጎትት እንዳይሆን ኅብረተሰቡንም አሳታፊ በሆነ መልኩ መስፈርቶች እየወጡ መሆናቸውን ተናግረዋል ተብሏል።



***የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግሥቱ፣ በሪፖርቱ ወቅት፤***

የኢፌዴሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በዚኹ ወር ባካሄደው 16ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በስድስተኛ ተረኛ አቅራቢነት ተመሳሳዩን የሥራ አፈጻጸሙን ያደመጠው **የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር**ን ሪፖርት ሲሆን፤ ሪፖርቱንም ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም በላይ አቅርበዋል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፈቲያ አህመድ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለቡዙ ዓመታት ሲንከባለሉ የነበሩ ፕሮጀክቶች ጥናት እና ዲዛይንን በሚመለከት 6 ፕሮጀክቶች ማጠናቀቁን በጥንካሬ አንስተዋል።

ከመስኖ መሠረተ-ልማት ግንባታ አንጻር ደግሞ ዐራት ፕሮጀክቶች የርክክብ ሥራ መሥራቱን በተጨማሪ ጥንካሬነት ያነሱት ሰብሳቢዋ፣ ከመስኖ ጥናት እና ዲዛይን አንጻር አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ፕሮጀክቶች ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ መናገራቸው ተዘግቧል። ከዚኽ ባለፈም፣ ጥናት እና ዲዛይናቸው አልቆ ግንባታቸው ያልተጀመሩ ፕሮጀክቶችን እና በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ፀጋዎችን በዕቅዱ አካቶ ፍትሓዊ በሆነ መልኩ ምላሽ ለመስጠት ትኩረት አድርጎ መሥራት ያስፈልጋልም ብለዋል ተብሏል።

አኹን ባለው ኹኔታ ነባር ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ ዶ.ር. አብርሃም በበኩላቸው፣ በቀጣይም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን በመለየት አቅም በፈቀደ መጠን ምላሽ ለመስጠት ጥረት እንደሚደረግ መናገራቸው ተሰምቷል።



***የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም በላይ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤***

በወርኃ ሚያዚያ፣ በጊዜ ምጣኔ ሰባተኛው የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራቱን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት** ሲሆን፤ ሪፖርቱንም

ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንደነበር ተዘግቧል። ለቋሚ ኮሚቴው የተቋማቸውን ሪፖርት ያቀረቡት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. ወርቁ ጋቸና ሲሆኑ፤ በሪፖርት ዘመኑ ኢንስቲትዩቱ ባለ 15 ፎቅ ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻን፣ ለስታርት-አፕ ሥነ-ምኅዳር የተመደበ ባለ 5 ፎቅ ሕንጻን እና ዘመናዊ የሰው ሠራሽ አእምሮ የኒፖድ የፈጠራ ማዕከልን ያካተተ የተራቀቀ የመሠረተ ልማት ሦሥትዮሽን ወደ ሥራ በማስገባት የኢትዮጵያን ዲጂታል ሉዓላዊነት በከፍተኛ ደረጃ አሳድጓል ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በግብርና፣ በትምህርት እና በፋይናንስ ዘርፎች ውጤታማ መረጃ የማሰባሰብ እና የመተንተን ሥራዎች መከናወናቸውንም ገልጸዋል። በሰው ሠራሽ አእምሮ እና በሮቦቲክስ የዘርፍ የወጣቶችን የፈጠራ ችሎታ ለማሳደግ ኢንስቲትዩቱ በአኹኑ ወቅት ለ200 ስታርት አፖች የተደራጀ የሥራ ቦታ እና የግብዓት ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ከዚኽ ባለፈም የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎትን ጨምሮ ዘጠኝ የሶፍትዌር መተግበሪያዎች ለምተው ወደ ሥራ የመግባት ምዕራፍ ላይ ይገኛሉም ተብሏል።

ሪፖርቱ አምስት ሀገር በቀል ቋንቋዎችን ከድምፅ ወደ ጽሑፍ ለመቀየር እና ለመተርጎም ለሚያስችሉ መተግበሪያዎች መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ጎን ለጎን፣ መላ የተሰኘ ሀገር በቀል የሰው ሠራሽ አእምሮ ሥርዓት መልማቱም ተጠቅሷል። የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግሥቱ፣ የኢንስቲትዩቱን የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ውጤታማ እና አርአያነት ያለው ሲሉ የገለጹት ሲሆን፣ ይኽም ከንድፈ-ሐሳባዊ አቅም ወደ ተጨባጭ እና ተግባራዊ ተጽዕኖ የተደረገ ሽግግር መሆኑን አመልክተዋል።



***የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተሩ ዶ.ር. ወርቁ ጋቸና፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤***

ይኸው የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በስምንተኛነት የበጀት ዓመቱን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸሙን ያደመጠው፣ **የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎትን** ሲሆን፤ ቋሚ ኮሚቴውም፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዲጂታላይዝድ እና ቀልጣፍ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ተቋሙ ያከናወናቸው ተግባራት አበረታች መሆናቸውን መግለጹ ተሰምቷል። በዲጂታላይዜሽን ክልሎችን ለማስተሳሰር እና አገራዊ ወጥ የመረጃ ቋት ለመፍጠር የተከናወኑ ሥራዎች ለሌሎች ተቋማት ተምሳሌት መሆኑን የተናገሩት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግሥቱ፣ ከ41 በላይ መንግስታዊ እና የፋይናንስ ተቋማት ጋር መረጃዎችን ለመለዋወጥ በጋራ የተሰሩት ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቁመዋል ተብሏል።

የሀሰተኛ ሰነዶች ቁጥር ወደ 95 በመቶ መቀነሱ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሰራው ሥራ አበረታች በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አክለው ያሳሰቡት ሰብሳቢዋ፣ ለረዥም ዘመናት በተቋሙ የሚገኙ ሰነዶችን ወደ ዲጂታል ለመለወጥ የተጀመሩ ሥራዎች በትኩረት መሥራት እንደሚገባም መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ፣ ኤጀንሲው ከ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን አሥተናግዶ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን የተናገሩት የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ሀሚድ ከኒሶ በበኩላቸው፣ ሰባት ክልሎች አገራዊ የመረጃ ቋት ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ወደ ሥርዓት ገብተዋል ብለዋል። አገልግሎቱን ወደ መሶብ አንድ ማዕከል በማስገባት እና ዜጎች ባሉበት ሆነው እንዲገለገሉ የሚያስችሉ ሥራዎች መከናወናቸውንም ዋና ዳይሬክተሩ አክለው መናገራቸው ተዘግቧል።



*የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት፣ የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎትን ሪፖርት ሲያደምጡ፤*

በኢንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ በዚኹ ሚያዚያ ወር **የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን** የ2018 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርትን ገምግሟል። በዘጠነኛነት የወሩ ተረኛ አቅራቢ የነበረውን የኮርፖሬሽኑን ያደመጠው የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ ግምገማው በዋናነት በፕሮጀክቶች አፈጻጸም፣ በፋይናንስ አሥተዳደር እና በዕዳ ክፍያ ስትራቴጂክ አቅዶች ላይ ትኩረት እንዳደረገ ጠቁመዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈ፣ የባቡር ዘርፉን በራስ አቅም ለመምራት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች እና የባለሙያዎችን አቅም የመገንባት ተግባራት ተጠናክሮ ሊሠራ እንደሚገባ ጨመረው ያስገነዘቡት ሰብሳቢው፣ የተገነቡ የባቡር መስመሮች፣ ባቡሮች እና ተያያዥ ንብረቶች እንዳይበላሹ እና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ኃላፊነት መወጣት እና መደበኛ ጥገና በማድረግ የመሠረተ-ልማት ደኅንነትን መጠበቅ እንደሚገባ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ ኮርፖሬሽኑ የአገሪቱን የትራንስፖርት ዘርፍ ለማዘመን የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የአመራር እና የቴክኒክ አቅሙን ማሳደግ እንደሚኖርበት ተናግረዋል ተብሏል። የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ኢንጂነር ሕሊና ጌታቸው በተራቸው፣ የአገር ሀብት የሆነውን የባቡር መስመር ከስርቆት እና ከአደጋ ለመከላከል ከፌዴራል ፖሊስ እስከ ክልል የደኅንነት መዋቅር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር

በቅንጅት እየተሰራ መሆኑ በሪፖርታቸው ወቅት መናገራቸው ተሰምቷል፡፡



*የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ኢንጂነር ሕሊና ጌታቸው፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የወሩ ዐሥረኛ የዚኹ በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን** ሲሆን፣ ሪፖርቱን ደግሞ ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕ/ር መሀመድ አብደም፣ ባለሥልጣኑ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የማሪታይም ሎጀስቲክ አገልግሎትን በማሳለጥ፣ በመከታተል እና በመቆጣጠር ውጤታማ ተግባራት ማከናወኑን ከመጥቀሳቸው ባለፈ፣ የሞጆ ደረቅ ወደብ በርካታ ጭነቶችን እንዲያስተናግድ ዘመናዊ እና ዲጅታላይዝ በሆነ መልኩ መገንባቱ አበረታች መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በሌላ መልኩ መርከቦች በሚፈለገው መልኩ ጭነቶችን ለማስተላለፍ ዓለም ዓቀፋዊ ነባራዊ ኹኔታው ተፅዕኖ መፍጠሩ በአጥረት እንደተገመገመ ሰብሳቢው አክለው ተናግረዋል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ ዘርፉ እንደ አገር ትኩረት ተሰጥቶት የተሻለ አፈጻጸም ያሳየ ተቋም መሆኑን አንስተው፣ ባለሥልጣኑ የገቢ እና ወጪ አማራጭን ከማስፋት አንፃር በጥናት ላይ ተመስርቶ ዲፕሎማሲን በማስፋት እየሰራ መሆኑ የሚበረታታ ነው ብለዋልም ተብሏል፡፡



*የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ፍራኦል ጣፋ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ፍራኦል ጣፋ በበኩላቸው፣ የመልቲ ሞዳል ሽፋንን ለማስፋት በሎጂስቲክ ዘርፍ የግሉን ተሳትፎ ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን ገልፀው፤ የባሕር ደኅንነት እና አደጋን ለመከላከል ዓለም ዓቀፍ ሕጉን መሠረት በማድረግ ከባሕር ማኅበራት ጋር በቅርበት እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ዳይሬክተሩ ለጥቀውም፣ ባለሥልጣኑ አጠቃላይ የገቢ እና ወጭ አገልግሎቱን ለማሳለጥ ከሎጀስቲክስ እና ትራንስፖርት ሚኒስቴር ተግባራት ጋር በማስተሳሰር፣ ሥርዓቱን ዲጅታላይዝ በማድረግ ደላላን በመከላከል የዋጋ ጭማሪን ለመቀነስ

ትኩረት ሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ለኮሚቴው አባላት መናገራቸውን መረጃው ያሳያል።

የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ የተነገረበት ኹነት ደግሞ፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽንን** የ2018 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በመገመበት ወቅት ነበር። የወርኃ ሚያዚያ ዐሥራ አንደኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረውን የዚኽን ተቋም ሪፖርት ያደመጡት፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ተቋሙ ከነበሩበት ችግሮች በመላቀቅ ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ተቋማዊ አደረጃጀቱ ላይ እና ተልዕኮው ላይ በማተኮር ውጤታማ ሥራዎች መሥራቱን አንስተው፤ ለውጥ እያስመዘገበ እንደሆነም ገልፀዋል ተብሏል።

ሰብሳቢው አክለውም በአገራችን እና በመላው ዓለም ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ የአደጋ ስጋቶች እየጨመሩ መሆኑን በማንሳት፣ ይሄንን የሚመጥን ምላሽ ለመስጠት በተቋም እና በመንግስት ደረጃ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል ብለዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ በበኩላቸው፣ ተቋሙ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በርካታ ውጤታማ ተግባራት ማከናወኑን ጠቁመው፣ ይኽንኑ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ብለዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ዶ.ር. ሽፈራው ተክለ ማርያም በበኩላቸው፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፈንድ በብሔራዊ ባንክ እና ንግድ ባንክ አካውንት ተከፍቶለት ፈንድ የማሰባሰብ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ ከየካቲት 1/2018 ዓ.ም. ጀምሮ ማሰባሰብ በተጀመረው በዚኹ ፈንድ፣ በአንድ ወር ወስጥ ከ 1.7 ቢሊየን ብር በላይ ማሰባሰብ መቻሉን ተናግረዋል። ከዚያ ባለፈም፣ በክልሎችም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ10 ቢሊየን ብር በላይ ማሰባሰብ መቻሉንም አክለውም መጥቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።



***የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ዶ.ር. ሽፈራው ተክለ ማርያም፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤***

በወርኃ ሚያዚያ፣ ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ በማለት፣ የዚኽኑ በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸማቸውን ካቀረቡት የፌደራል ተቋማት መካከል፣ **የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን** ይገኝበታል። በጊዜ ምጣኔ

የወሩ ዐሥራ ኹለተኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረውን የዚኽን ተቋም ሪፖርት ያደመጠው ደግሞ፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱም፣ የተጀመረው የተቋም ግንባታ በአህጉር እና በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ እየሆነ የመጣ ተቋም መሆኑን ገልጸው፣ ተቋሙ የሠራቸውን መልካም ሥራዎች ይበልጥ አጠናክሮ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

ተቋሙ የተቋማትን፣ የመሠረተ ልማት ጥበቃ እንዲኹም ሃይማኖታዊ በዓላት በሚገባ ተጠብቀው ማኅበረሰቡ ያለምንም ሥጋት ባህሉን፣ ወጉን እና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ፈጽሞ በሰላም ወደ ቤቱ እንዲመለስ የተሰራው ሥራ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ያሉት ሰብሳቢዋ፤ ጸረ-ሰላም ኃይሎችን፣ ሕገ-ወጦችን፣ ኮንትሮባንዲስቶችን እና ወደ ተለያዩ የዓለም አገራት ሰዎችን በሚያዘዋውሩ አካላት ላይ እየተወሰደ ያለው ዕርምጃ ሊበረታታ እንደሚገባ እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመናበብ ለፈጸሙት ድርጊት አሥተማሪ ቅጣት እንዲሰጣቸው ተጠናክሮ መሰራት አለበት ብለዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፣ ወንጀል ምርመራ ላይ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ መሥሪያ ቤቱ የሰራው ሥራ ሊበረታታ የሚገባ እና ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገብረ ሚካኤል በበኩላቸው፣ ተቋሙ በዘጠኝ ወራት ውስጥ በሽብርተኝነት እና በተደራጁ የወንጀል ተግባራት የተሰማሩ አካላትን በከፍተኛ ኃላፊነት ሕግ እና ሥርዓትን ለማስከበር የሚያስችል አቅም የፈጠረ ተቋም መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

ተቋሙ፣ ኢትዮጵያ ሕዝባዊ በዓላት እና ዓለም ዓቀፋዊ ሁነቶች ያለምንም የጸጥታ ችግር ማስተናገድ እንደምትችል በተግባር በማስመስከር የአገራችን ገጽታ በመገንባት ረገድ የበኩሉን ድርሻ መወጣቱን አክለው ያነሱት ጄኔራሉ፣ አገራዊ ምርጫው በሰላም እንዲጠናቀቅ እቅድ በማዘጋጀት በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ በመታገዝ የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑንም መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀኔራል ደመላሽ ገብረ ሚካኤል፣ የኮሚሽኑን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትን፤** የተመሳሳዩን በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም መገምገሙም፣

ኢንሲቲቲዩትን የወሩ ዐሥራ ሦሥተኛ ሪፖርት አቅራቢ ተቋም አድርጎታል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕ/ር መሀመድ አብዶ፣ ኢንስቲቲዮቱ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እያከናወነ ያለው አፈጻጸም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አቅጣጫ ሰጥተዋል ተብሏል።

ከዚያ ባለፈም፣ ኢትዮጵያ ለኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚውሉ ከውጭ አገራት የምታስገባቸውን ግብዓቶች በአገር ውስጥ ለመተካት የሚከናወኑ የጥናት እና ምርምር ስራዎች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ እና የውጭ ምንዛሬን ማዳን እንዲቻል የተጀመሩ ጥረቶች ሊጠናከሩ እንደሚገባም ሰብሳቢው ጨምረው መናገራቸው ተጠቅሷል።



*በከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ታምራት ሙሉ፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የኢንስቲቲዩቱ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ታምራት ሙሉ በበኩላቸው፣ የኮንስትራክሽን ዘርፉን በማዘመን የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ለማድረግ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገራት ዩኒቨርሲቲዎች እና ተቋማት ጋር የተቀናጀ ሥራ እየተሰራ በመሆኑ ተጨባጭ ውጤቶች እየታዩ እንደሆነ ከመጥቀሳቸው ባለፈ፣ ኢንስቲትዩቱ ተቋማዊ ማሻሻያ እና መደበኛ ሥራዎችን ጎን ለጎን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ እያከናወነ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተዋል ተብሏል።

የወሩ ዐሥራ ዐራተኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የኢትዮጵያ ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን** ሲሆን፣ የተቋሙ የበጀት ዓመቱን የዘጠኝ ወራት ሪፖርት ያደመጠው ደግሞ፣ በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። ኮርፖሬሽኑ በስሩ በሚገኙት የሙገር ሲሚንቶ፣ አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ማዘጋጃ፣ ዐዋሽ መልካሳ ኬሚካል እና ባቱ ኮስቲክ ሶዳ ባሉ ግዙፍ ፋብሪካዎቹ አማካኝነት፣ በአገሪቱ በኬሚካል ዘርፍ ያለውን የገበያ ክፍተት ለመሙላት እና ለዘርፉ እድገት አሥተዋጽዖ እንዲያደርግ በማለም የተቋቋመ እንደሆነ የተናገሩት ደግሞ፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና እንደነበሩ ተዘግቧል።

ሰብሳቢው አክለውም፣ ጤናማ የሀብት አጠቃቀምን ማረጋገጥ፣ ወጪን በመቀነስ ትርፋማነትን ማሳደግ እና የውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ ወቅቱን የጠበቀ የሒሳብ ምርመራ ማስደረግ እና በተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ የሚሉት ዋና ዋና ነጥቦች በጥልቀት እንደተገመገሙ መናገራቸው ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ

በበኩላቸው፣ ኮርፖሬሽኑ በቀጣይነት በሚሰራቸው ሥራዎች የአገሪቱን ኹለንተናዊ ዕድገት ከግምት ያስገቡ እንዲኹም በጥናት እና ምርምር የተደገፉ ሥራዎችን በመስራት የተሻለ እምርታ እንዲያስመዘግብ መስራት ይገባል ብለዋል ተብሏል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ዶ.ር. ኢንጂነር ሁንዴሳ ደሳለኝም በሪፖርታቸው፣ ኮርፖሬሽኑ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ 9 ወራት ውስጥ 4.6 ቢሊዮን ብር ገቢ እና 725.28 ሚሊዮን ብር ያልተጣራ ትርፍ ማግኘት መቻሉን ጠቅሰዋል። የኮርፖሬሽኑ ገቢ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ6.40 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን ያነሱት ሥራ አሥፈጻሚው፣ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ የተመዘገበው ውጤትም የዕቅዱን 77.27 በመቶ ያህል ማሳካት መቻሉን ገልጸዋል።



***የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት፣ የኮርፖሬሽኑን ሪፖርት ሲያደምጡ፤***

የግብዓት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ፣ እንዲኹም በመካከለኛው ምሥራቅ ከተከሰተው ጦርነት ጋር ተያይዞ የመጣው የነዳጅ እና የግብዓት ዋጋ መናር ዋነኞቹ ተግዳሮቶች እንደነበሩም፣ ሥራ አሥፈጻሚው አክለው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የገንዘብ ሚኒስቴርን** የዚኽኑ በጀት ዓመት የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ማድመጡም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የወሩ ዐሥራ አምስተኛ ሪፖርት አቅራቢ ተቋም አድርጎታል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ በሰጡት አሥተያየት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአገሪቱን የበጀት ጉድለት በራስ አቅም ለመሙላት እና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የሚያደርገው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል በማለት አሥገንዝበዋል ተብሏል።

የእዳ ሽግሽግ እና የብድር ጫናን ለመቀነስ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት እንዲኹም ከልማት አጋሮች ጋር ያለው መልካም ግንኙነት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ያሉት ሰብሳቢው፣ ከካፒታል በጀት እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታየው ችግር አኹንም ትኩረት ይፈልጋል ብለዋል። የገንዘብ ሚኒስትሩ የተከበሩ አህመድ ሽዴም፣ በዋና ዋና የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ በማተኮር የዋጋ ንረትን በማረጋጋት ወደ አንድ አሃዝ ማውረድ መቻሉን፣ የበጀት ጉደለትን በራስ አቅም ለመሸፈን የተደረውን ጥረት፣ የብድር ጫናን ለመቀነስ ከልማት አጋሮች ጋር የተፈጠረውን መልካም ግንኙነት እና የፊስካል ፖሊሲውን አተገባበር አሥመልክተው ማብራሪያ መስጠታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ሚኒስትሩ አክለውም፣ አጠቃላይ የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን፣ እንዲኹም ከግብር አሰባሰብ አኳያ በበጀት ዓመቱ 9 ወራት የተሰበሰበው ገቢ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ7.8 በመቶ እድገት ማሳየቱን እና ይኽንኑም አጠናክረው የሚቀጥሉ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል፡፡



***የገንዘብ ሚኒስትሩ የተከበሩ አህመድ ሽዴ፣ ሪፖርታቸውን ባቀረቡበት ወቅት፤***

የሚያዚያ ወር ዐሥራ ሥድስተኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው የፌደራሉ ተቋም፣ **የጤና ሚኒስቴር** ሲሆን፤ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የዚኽን በጀት ዓመት የ9 ወራት ሪፖርት ያደመጠው ደግሞ፣ በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል።

የጤና ሚኒስቴር ከክልል ጤና ቢሮዎች እስከ ተጠሪ ተቋማት ድረስ ያለውን የሥራ ግንኙነት በቅንጅት እያከናወነ መሆኑን የተናገሩት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወርቀሰሙ ማሞ፣ ተቋማዊ ሥርዓትን በመገንባት እና ዲጂታላይዜሽን ሥርዓቱን በማዘመን ረገድ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባም አሳስበዋል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተቋማት ሥርዓት ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ፣ እስከ አኹን በዋና ዋና ተግባራቱ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች ማስቀጠል እንደሚቻል መናገራቸው ተሰምቷል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ በበኩላቸው፣ የጤና ፖሊሲው ቅድመ መከላከል ላይ ያተኮረ መሆኑ የማርበርግ ወረርሽኝን በሙሉ ለመቆጣጠር ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳበረከተ ጠቅሰው፤ ወረርሽኙን በመቆጣጠር የተመዘገበው ስኬት ለሌሎች አገራት እና ለዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ጭምር ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ ተሞክሮ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል። የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ዶ.ር. መቅደስ ዳባም፣ በክልሎች እና በፌዴራል ደረጃ የሚገነቡ የጤና ተቋማት ፕሮጀክቶች ትኩረት ሰጥቶ በመደገፍ በጊዜ እና በጥራት እንዲጠናቀቁ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ደረጀ ድጉማ በበኩላቸው፣ ኤች አይ ቪ ካለባቸው እናቶች ለተወለዱ ሕፃናት የሚሰጠው የቅድመ መከላከል ሕክምና 88 በመቶ ታቅዶ 73 በመቶ ብቻ መፈጸሙን ጠቅሰው፤ ይኽም የሆነው የግብዓት አቅርቦት መቋረጥ እና ሪፖርት በአግባቡ አለመላክ ጋር ተያይዞ መሆኑን ለኮሚቴው አብራርተዋል።



*የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ዶ.ር. መቅደስ ዳባ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

**የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅትም፣** የዚኹ ወር ተረኛ ሪፖርት አቅራቢ ነበር። በጊዜ ቅደም-ተከተል ዐሥራ ሰባተኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው የዚኽን ተቋም የ9 ወራት ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መናም፣ የተቋሙ የ9 ወራት እቅድ አፈጻጸም ግልጽ፣ ተዓማኒ እና የአመራር ቅንጅት የታየበት ነው ብለዋል ተብሏል።

ተቋሙ ቀደም ሲል በከባድ ችግር ውስጥ እንደነበር ያነሱት ሰብሳቢው፣ የአመራር ለውጥ በማድረግ ከዚያ ኹኔታ መውጣቱን እና አኹን በተሻለ ኹኔታ እየሠራ መሆኑን ጨምረው መግለጻቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ ተቋሙ ከቋሚ ኮሚቴው ጋር ይበልጥ በመተባበር ለለውጥ የሚሠራ መሆኑን ገልፀው፣ ችግሮችን በጥናት፣ በዘላቂነት እና በአስተማማኝ መልኩ ከሥር መሠረቱ ለመፍታት በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ያስጠናቸው ጥናቶች ጥሩ መሆናቸውን ገልፀዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አሥፈጻሚው ዳዊት አዳነም፣ ድርጅቱ ብቃት ባለው የሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሠራር ሥርዓት፣ ጠንካራ የአቅርቦት እና የግብይት ሰንሰለት በመገንባት፣ ጥራታቸውን የጠበቁ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማልማት እና በማቅረብ የአገሪቱ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጤታማነት እንዲጨምር እና የገበያ መረጋጋት እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረገ መሆኑን ገልፀዋል።



*የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለስ መና በተቋሙ ሪፖርት ወቅት፤*

በዚኽ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የፌደራል ተቋማቱን የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸም በስፋት በገመገሙበት ወር፣ በዐሥራ ስምንተኛነት ሪፖርቱን እንዲያቀርብ የተጠራው፣ **የኢትዮጵያ ልማት ባንክ** ሲሆን፤ የባንኩን ሪፖርት ያደመጠውም፣ በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ ባንኩ ለአገሪቱ

ምጣኔ ሀብት የጀርባ አጥንት ከመሆንም ባሻገር የሚሰጣቸው ብድሮች የአካባቢ ልማትን የሚያነቃቁ በመሆናቸው በአገሪቱ ልማት ላይ የራሱን አሻራ ያኖረ ነው ሲሉ መናገራቸው ተዘግቧል።

ባንኩ ማነቆ የሆኑ ፖሊሲዎችን ወደፊት ሊያሰራ በሚችል መልኩ ማሻሻሉ፣ የብድር አመላለሱ የተሻለ መሆኑ፣ ከውጭ ምንዛሪ ግኙት ጋር ተያይዞ የተሰሩ ሥራዎችን እንዲኹም ሌሎች የተሻሉ ሥራዎችን በመሥራቱ የባንኩ ገቢ እየተሻሻለ መምጣቱን ሰብሳቢው በጥንካሬ ጎኑ ማንሳታቸውም ተሰምቷል። የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ኢሳያስ ካሳ በበኩላቸው፣ ከብድር አሰጣጥ ሂደቶች ጀምሮ ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላት ስትራቴጂ ነድፈው እየሰሩ እንደሆነ አንስተው፣ የባንኩን መሠረታዊ ችግሮች ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ አዲስ ቦርድ ተቋቁሞ ወደ 23 ፖሊሲዎች ፀድቀው የተለየ ክትትል በማድረግ የልማት አጋሮች ቋሚ የሆነ ፈንድ ሞብላይዜሽን በማቋቋም ሥራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ጠቁመዋል ተብሏል።



*የኢትዮጵያ ልማት ባንኩ ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ኢሳያስ ካሳ፣ የባንኩን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

**የገቢዎች ሚኒስቴር**፣ በገቢ አሰባሰብ፣ በአሠራር እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከፍተኛ ለውጥ እያሳየ ስለመሆኑ የተነገረበት ኹነት ደግሞ፣ ሌላይኛው የወሩ የሥራ አሥፈጻሚ ተቋማት ክትትል ክንውን ነበር። የወሩ ዐሥራ ዘጠነኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው የገቢዎች ሚኒስቴርን የዚኽን በጀት ዓመት የ9 ወራት ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ኮሚቴ መሆኑም ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል ከቋሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ግብረ መልስ ተቀብሎ ወደ ተግባር በማዋል ረገድ ለሌሎች ተቋማት አርአያ መሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

ሰብሳቢው ለጥቀውም፣ በዘንድሮው አመት የተሰበሰበው ገቢም አምና ከነበረው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ 449 ቢሊየን ብር ጭማሪ እንዳለው ከመጥቀሳቸው ባለፈ፣ ለገቢው መሻሻልም ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ የተሰሩ ሥራዎች፣ የአመራር እና የሠራተኛው ቁርጠኝነት፣ ለግብር ከፋዩ የተሰጠው እውቅና እና የማበረታቻ ሽልማት መነሳሳት እንደፈጠረ መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በተራቸው፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እቅዱን ሙሉ በሙሉ በማሳካት ከሌሎች ተቋማት የተሻለ መሆኑን አንስተው፣ለዚኽም በምክር ቤቱ የተደረጉ የሕግ ማሻሻያዎች ትልቅ ውጤት ማምጣታቸውን እና ተቋሙም ሕጋግቱን ወደ ተግባር

ማዋሉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው ብለዋል ተብሏል። የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው ሚኒስቴሩ በገቢ አሰባሰብ፣ በአሠራር እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም አኹን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ የሆነ ክትትል እና ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸውን አንስተው፣ ሚኒስቴሩ በ2018 በጀት ዓመት ታላቅ አገራዊ ተልዕኮ ወስዶ በመፈጸም ላይ የሚገኝ ተቋም መሆኑን ጨመረው ጠቁመዋል ተብሏል።



*የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፣ የተቋማቸውን ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤*

ወርኃ ሚያዚያ ሃያኛ እና የመጨረሻው ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የውኃ እና ኤነርጂ ሚኒስቴር** ሲሆን፣ የተቋሙን የዚኽን በጀት ዓመት የ9 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያደመጠውም፣ በምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወይዘሮ ፈቲያ አህመድ፣ የአገሪቱ የውኃ ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ፣ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ክትትል ሽፋን ማደጉ፣ የገጠር እና የከተማ የንጹሕ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመሩ፣ እንዲኹም ኤሌክትሪክ በማይደርስባቸው አካባቢዎች የሶላር ኢነርጂ ሽፋን እያደገ መምጣቱን በጥንካሬ ጎንነት አንስተዋል ተብሏል።

ሰብሳቢዋ አክለውም፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕሮጀክቶች፣ የአንዳንድ ከተሞች የንጹሕ ውኃ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እና ድርቅ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች እየተሠሩ ያሉት ሥራዎች አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆናቸውን መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በበኩላቸው፣ የንጹሕ መጠጥ ውኃ ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢሆንም በአንዳንድ አካባቢዎች የተነሱ የንጹሕ ውኃ ችግሮችን ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አስረድተዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች የሚስተዋለውን የኤሌክትሪክ ተደራሽነት እና መቆራረጥ ችግርን ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች የሚስተዋለው ስርቆት ግን ተግዳሮት እንደሆነባቸው መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።



*የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወይዘሮ ፈተያ አህመድ፣ በሪፖርቱ ወቅት፤*

## 2.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኙቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ወርኃ ሚያዚያን ያጠናቀቀው ሕግጋት በማውጣት እና የተቋማትን ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም አልነበረም፤ ከዚያ ተሻገሮም በዛ ያሉ ተቋማትን በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ሲጎበኝ፣ የተወሰኑ የመስክ ጉብኙቶችንም አድርጓል።

### 2.2.1 የተቋማቱ ጉብኙቶች

በወርኃ ሚያዚያ የመጀመሪያዎቹ ቀናት፣ በእንደራሴዎቹ በመጎብኘት ቀዳሚ የሆነው ተቋም፣ **የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር** ሲሆን፣ የመስክ ምልከታውን ያደረገውም በምክር ቤቱ የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ኘ/ር መሐመድ አብዶ በጉብኙቱ ወቅት እንደገለጹት፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ዘርፉ ሳይዘምን የኢኮኖሚ እድገት አይታሰብምና፣ ይኽን ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት ዘርፉን እንደገና አደራጅቷል ብለዋል፡፡

ይኽም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመጪው ጊዜ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፍላጎትን ለመመለስ የተዘጋጀ ያደርገዋል ያሉት ሰብሳቢው፣ ከዚህ አንፃር እየተሰራ ያለው ሥራም ተስፋ ሰጪ ነው ብለዋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ተቋሙ በተቋም ግንባታ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ተግባራት የተሰጠውን ኃላፊነት በመፈጸም፣ በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማትን ጨምሮ አገልግሎቱን ለማሻሻል ዲጂታላይዜሽን ላይ የተሰሩ ሥራዎች ጥሩ መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል፡፡

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ዓለሙ ስሜ በበኩላቸው፣ አሁን በተከሰተው ዓለም ዓቀፋዊ ሁኔታ በተከሰተው የነዳጅ አቅርቦት ምክንያት የትራንስፖርት ዘርፉ ችግር እንደገጠመው ጠቅሰዋል፡፡ ሚስትሩ አክለውም፣ አኹን ላይ የትራንስፖርት ዘርፉ እንዳይቋረጥ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ልዩ ኮማንድፖስት ዐዋቅሮ ሰፊ ሥራ እየሰራ መሆኑንም በእዚያ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት አንስተውላቸዋል ተብሏል።



*ቋሚ ኮሚቴው፣ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርን በጎበኘበት ወቅት፤*

በኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን** መሥሪያ ቤት ያደረገው የመስክ ምልከታ ሌላይኛው የወሩ ክንውን ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዮሓንስ መስፍን፣ ተቋሙ የፋይናንስ አካታችነትን እና ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲዳብር የሚያደርግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር፣ የመንግስትን ሕግ እና ሥርዓት ተከትሎ እየሰራ መሆኑ፣ ሴቶችን የማብቃት ሥራው ጥሩ መሆኑን እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራቱ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተሯ ሐና ተኽልቁ በበኩላቸው፣ ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን በዘመናዊ አሠራር፣ በጥቆማ እና የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶችን በማድረግ የመቆጣጠር ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ዳይሬክተሯ ለጥቀውም፣ በ2018 በጀት ዓመት በጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ እና የቁጥጥር ሥርዓት የሚመራ የካፒታል ገበያ እንቅስቃሴ እንዲኖር፣ ዘመናዊ የገበያ መሠረተ ልማቶች በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲውሉ፣ ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች በንቃት እንዲሳተፉ እና አዳዲስ አግልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ እንዲወስዱ እየተደረገ መሆኑንም ገልጸዋል ተብሏል።



*ቋሚ ኮሚቴው፣ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣንን በጎበኘበት ወቅት፤*

በወርኃ ሚያዚያ፣ በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙት ተቋማት መካከል ማሳያ የሚሆነው ሌላይኛው ተቋም፣ **የኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ** ሲሆን፤ ዩኒቨርሲቲውን የጎበኘው በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፤ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ዩኒቨርሲቲው የጀመረውን ተቋማዊ ማሻሻያ አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባው አሥገንዝቧል ተብሏል። ማሻሻያው የታለመለትን ግብ እንዲመታ የዩኒቨርሲቲው አመራር በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለበት የተናገሩት ደግሞ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ ሲሆኑ፤ ሰብሳቢው አክለውም፣ ዩኒቨርሲቲው በአገር እና ዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው ማሻሻያውን በፍጥነት ማስኬድ እንደሚገባ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።

የዩኒቨርሰተው ፕሬዘዳንት ዶ.ር. ንጉስ ታደሰ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው ከአኹን ቀደም የነበሩበትን ችግሮች ለመፍታት ጠንካራ የማሻሻያ ሥራ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ዩኒቨርሲቲው የመንግስትን

አገልግሎት እና አሥተዳደር ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ ተልዕኮ ሰንቆ እየሰራ መሆኑን ያብራሩት ኘሬዚዳንቱ፣ ማሻሻያውን ለማሳካት ምቹ ኹኔታ መኖሩንም ጨምረው ተናግረዋል ተብሏል።



*የሰው ኃብት ልማት፤ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ በተቋሙ ጉበኝት ወቅት፤*

በዚኹ ወርኃ ሚያዚያ፣ ወደ **የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርኘራይዝ** የደረሱት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኢንተርኘራይዙን አኹናዊ ኹኔታ ተዘዋውረው ተመልክተዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች የአገር ዕድገት የማፋጠን እና የሕዝቡን የልማት ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሚናቸውን በአግባቡ ለመወጣት ስትራቴጂካዊ እቅድ ቀርፀው ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባቸው አሳስበዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈ፣ ኢንተርኘራይዙ አሰራሮችን በማዘመን እና ዲጂታላይዝድ በማድረግ ከሰው ንክኪ ነፃ በማድረግ ወቅቱን የሚመጥን አገልግሎቶች መስጠት እንደሚጠበቅበት የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ የመንግስት ሀብት እና ንብረትን በአግባቡ በማሥተዳደር እና ዘመናዊ የፋይናንስ አሠራርን በመከተል ብልሹ አሰራሮችን ማረም እንደሚገባም ጨምረው ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርኘራይዝ ዋና ሥራ አሥፈጻሚ ሙስጠፋ አባሲመል በበኩላቸው፣ የአገሪቱን ትራንስፖርት በማሳለጥ የመንገዶች ደኅንነትን በማስጠበቅ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን ከመጥቀሳቸው በተጨማሪ፣ የፍጥነት መንገዶች የአገርን ገቢ እና ወጪ ምርቶችን በማሳለጥ ለአገር ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ትልቅ አሥተዋጽዖ እያደረጉ መሆናቸውን ወደ ተቋማቸው ለደረሱት የቋሚ ኮሚቴው አባላት አሥረድተዋል።



*ቋሚ ኮሚቴው፣ የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርኘራይዝን ሲጎበኝ፤*

እንደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ወርኃዊው መረጃ ከሆነም፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **በኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት** መሥሪያ ቤት ምልከታ አድርገው ነበር። ቋሚ ኮሚቴውም፣ የኢሚግሬሽን እና ዜግነት

አገልገሎት ዋና መሥሪያ ቤት፣ በጥራት እና በበቃት የቪ አይፒ እና የአሥቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን በጉብኝቱ አረጋግጧል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ በተሰራው ተቋማዊ ማሻሻያ፣ የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ከነበሩበት ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተላቆ ተጨባጭ ስኬት ማስመዝገብ እንደቻለ ገልፀዋል። ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ ተቋሙ በመላ አገሪቱ ባሉት ከ30 በላይ ቅርንጫፎች ተገቢውን አገልግሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ለኅብረተሰቡ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ተጨማሪ ግንዛቤ ሊፈጠር እንደሚገባም አሳስበዋል ተብሏል።

የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተሯ ሠላማዊት ዳዊት በበኩላቸው፣ ተቋሙ ማሻሻያውን ሲከውን፣ ሕግጋት እንዲሻሻሉ እና ሌሎች መሠረታዊ ነገሮች እንዲሟሉ የቋሚ ኮሚቴው አገዛ ቀላል እንዳልነበረ አስታውሰው፣ አኹን ላይ ተቋሙ ዓለም ዓቀፍ ስታንዳርዱን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጎሣ ደምሴ በተራቸው፣ በተሰራው ተቋማዊ ማሻሻያ፣ ተቋሙ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት እንደተቻለ መጥቀሳቸውም ተዘግቧል።



***ቋሚ ኮሚቴው፣ በኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት መሥሪያ ቤት ተቋማዊ ምልከታ ባደረገበት ወቅት፤***

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተጎበኘው **የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕም፤** ሌላው የወሩ ማሳያ ተጎብኚ ተቋም ነበር። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የቡድኑ ሰብሳቢ የተከበሩ ደረጀ ደበላም፣ የምልከታው ዋና ዓላማ በኦዲት ሪፖርት የተጠቀሱ ምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና የተቋማዊ ሥርዓት ማሻሻያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መሆኑን መናገራቸው ተጠቅሷል።

የቋሚ ኮሚቴው አባል የተከበሩ ወ/ሮ ሱመያ ደሳለው በበኩላቸው፣ ከ2013 እስከ 2016 ዓ.ም. ድረስ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት ናሙና ተወስዶ የተሰራባቸው 19 ነጥቦች እንደነበሩ ገልፀው፤ ኦዲት በተካሄደበት ወቅት ከነበረው፣ አሁን ላይ ተቋሙ የተሻለ አፈጻጸም እንዳለው እና ይኽም ሊበረታታ የሚገባ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። እንደራሴዋ አክለውም፣ ምክር ቤቱ በዐዋጅ ይኽንን ተቋም እንደገና ማቋቋም እንዳለበትም አመላክተዋል።

የኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢኪዩፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ ዋና ሥራ አሥኪያጅ ያደኑ ትርፌሳ በበኩላቸው፣ በክዋኔ ኦዲት ግኝት የደነበኛ እርካታ ጥናት በውስጥ እና በውጭ አጥኚዎች የሚጠና መሆኑን አመላክተዋል ተብሏል። ከዚኽ በፊት በሦሥተኛ ወገን ተጠንቶ በታዩት ክፍተቶች ላይ እየተሰራ መሆኑን ያነሱት ሥራ አሥኪያጁ፣ ምርቶችም በዓለም ዓቀፍ ስታንዳርድ የሚመረቱ እና ደንበኞችም መጠቀም የሚችሉት በዚኽ አግባብ ብቻ በመሆኑ የነበረው የአሰራር ሥርዓት ችግር ተፈቷል ማለታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።




*ቋሚ ኮሚቴው፣ የኢትዮ- ኢንጂነሪንግ ግሩፕን በጎበኙበት ወቅት፤*

**የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ** የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እና የተማሪዎችን አገልግሎት ለማዘመን የጀመራቸው ሰፋፊ የሪፎርም ሥራዎች ተስፋ ሰጪ በሆነ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የተነገረበት ክንውንም፣ አንዱ የወሩ ማሳያ የተቋማት ጉብኝጥ ነበር። ጉብኝቱን ያካሄደው፣ በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮም፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የአገሪቱን የትምህርት ጥራት በመመለስ ረገድ የላቀ ታሪካዊ ኃላፊነት ያለበት ተቋም መሆኑን ጠቅሰው፣ ይኽንንም እውን ለማድረግ የጀመራቸው የማሻሻያ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ተናግረዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው በበኩላቸው፣ አንጋፋው ዩኒቨርሲቲ በበርካታ ተግዳሮቶች በማለፍ አገራዊ ተልዕኮውን እየተወጣ ያለ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መሆኑን ጠቅሰው፣ ይኽንን ስኬት አጠናክሮ ለማስቀጠል ባለድርሻ አካላት መረባረብ እንዳለባቸው ማስገንዘባቸው ተሰምቷል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ተሾመ ነቃ-ጥበብ በተራቸው፣ ዩኒቨርሲቲው ከአሁን በፊት የነበሩበትን ውስጣዊ እና ውጫዊ ማነቆዎች እየፈታ አገራዊ ተልዕኮውን እየተወጣ እንደሚገኝ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተውላቸዋል። የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ.ር. ቴዎድሮስ ሙሉጌታም፣ የዩኒቨርሲቲውን የለውጥ ሥራዎች ያቀረቡ ሲሆን፥ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ የለውጥ ጉዞ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል ተብሏል።



***ቋሚ ኮሚቴው፣ የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲን በጎበኘበት ወቅት፤***

### 2.2.2 የመስክ ጉብኝቶች

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሚያዚያ፣ እንደራሴዎቹ ካደረጓቸው የመስክ ጉብኝቶች በቀን ምጣኔ በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው፣ በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ **በሸገር ከተማ** ያካሄደው የመስክ ጉብኝት ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌም፣ በግብርናው ዘርፍ የተሰሩ ሥራዎችን በመገምገም ጠንካራ ጎኖች እንዲቀጥሉ እና ውስንነት የሚታየባቸው ጉዳዮች እንዲሻሻሉ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በግብርናው ዘርፍ የሚሰሩ ሥራዎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲኹም የአገር ውስጥ ገቢን እና የውጭ ምንዛሬን ማሳደግ የዘርፉ ዋና ትኩረት እንደሆነም ሰብሳቢው አሥታውቀዋል ተብሏል። የሸገር ከተማ ምክትል ከንቲባ እና የግብርና ልማት ክላስተር አሥተባባሪው ግርማ ኃይሉ በበኩላቸው፣ ከቋሚ ኮሚቴው የቀረበላቸውን ምክር ሐሳብ ተቀብለው በቀጣይ በግብርናው ዘርፍ የተጀመሩትን የልማት ዕቅዶች አጠናክረው እንደሚያስቀጥሉ ገልጸዋል ተብሏል።



***ቋሚ ኮሚቴው፣ በሸገር ከተማ የመስክ ጉብኝት ወቅት፤***

ሌላይኛው ተጠቃሽ የወሩ የመስክ ጉብኝት የተካሄደው **በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ** ሲሆን፣ የመስክ ምልከታውን ያካሄደውም በምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬም፣ ከፋብሪካው የሚወጡ ተረፈ ምርቶችን ጥቅም ላይ በማዋል አካባቢን ለመጠበቅ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የሚበረታቱ መሆናቸውን እና ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸዋል ተብሏል።

የፍሳሽ ቆሻሻንም በአግባቡ በማጣራት የሚለቀቅ መሆኑ ጥሩ መሆኑን ጨምረው ያነሱት ምክትል ሰብሳቢው፣ በቀጣይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ጥናት በማድረግ ከሽታ ጋር በተያያዘ የሚስተዋለውን ችግር ለመቀነስ አስፈላጊው ሥራ መከናወን እንዳለበት ጠቁመዋል።

የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሥራ አሥኪያጅ ኤርሚያስ ወሰኑ በበኩላቸው፣ እንደ ድርጅት አካባቢን በጠበቀ መልኩ ለመሥራት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከፋብሪካው የሚወጡ ተረፈ ምርቶችን ወደ አፈር ማዳበሪያ፣ ለኬሚካል መሥሪያ እና ለሌሎችም ጥቅም ላይ በማዋል አካባቢን ለመጠበቅ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን በዚያ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተዋል ተብሏል።



*ቋሚ ኮሚቴው፣ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካን ሲጎበኝ፤*

የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ በዚኹ ሚያዚያ ወር **በኢትዮጵያ አየር መንገድም** የመስክ ጉብኝት አካሂደው ነበር። የመስክ ጉብኝቱን የከወነው በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ በምልከታው ወቅትም፣ በቢሾፍቱ አዲሱ ዓለም ዓቀፍ ኤርፖርት ፕሮጀክት ያለበት አጠቃላይ ኹኔታን አስመልክቶ፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ሥራ አሥፈፃሚ መስፍን ጣሰው አማካኝነት ማብራሪያ ተደርጎለታል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ መለሰ መናም፣ የቢሾፍቱ አዲሱ ዓለም ዓቀፍ ኤርፖርት ፕሮጀክት የኢትዮጵያን ገጽታን የሚገነባ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ በአቪዬሽን፣ በንግድ እና በኢኮኖሚ ዘርፍ ያላትን ትልቅ አቅም ይዞ ወደ ቀጣይ የዕድገት ምዕራፍ ለመሻገር የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። ከቦታው የተነሱ አርሶ አደሮችን መልሶ ለማቋቋም የታቀዱ እቅዶች ተቋሙን የሚመጥኑ መሆናቸውን አክለው ያነሱት ሰብሳቢው፣ አርሶ አደሮቹ በአዲሱ አካባቢ እስኪቋቋሙ ድረስም የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባም ማሳሰባቸው ተሰምቷል።



*ቋሚ ኮሚቴው፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ጉብኝቱ ወቅት፤*

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ አየር መንገዱ ከፍ ያለ ተቋም መሆኑን አንስተው፣ የአፍሪካ እና የብልፅግና ተምሳሌት መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ሥራ አሥፈፃሚው መስፍን ጣሰው በተራቸው፣ በቢሾፍቱ አካባቢ የሚገነባው አዲሱ ዓለም ዓቀፍ ኤርፖርት ፕሮጀክት 3808 ሄክታር መሬት በመረከብ የግንባታ ሂደቱን ጀምሯል ብለዋል። ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኞች አቅምን በእጅጉ እንደሚያሳድግ እና ኢትዮጵያ በአፍሪካ የአቪዬሽን ማዕከል ያላትን ቦታ የበለጠ ያሳድጋል

ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

## 3. የፓርላማው ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በዚኹ ሚያዚያ ወር ካከናወናቸው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ መካከል አንዱ፣ በምክር ቤቱ **የኢትዮ-ኢጋድ እና የምሥራቅ አፍሪካ አገራት የፓርላማ የዲፕሎማሲ ቡድን አባላት፣ ከሶማሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና የሶማሊያ አምባሳደር ጋር** ያካሄዱት ቀጠናዊ ውይይት ነበር። በኹለቱ አገራት መካከል በፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ በሠላም እና በባህል ዙሪያ የተደረገው ውይይት የተካሄደው በሶማሊያ ኢምባሲ ሲሆን፣ የኢትዮ-ሶማሊያን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማጠናከር ሰፊ ውይይት መደረጉም ተገልጿል።

የፓርላማ ዲፕሎማሲ የወዳጅነት ቡድኑ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ መስፍን እርካቤ፣ የኢትዮ-ሶማሊያን ግንኙነት እንዲኹም ኹለቱ አገሮች በኢጋድ አባልነታቸው የሚያደርጉትን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በሠላም እና ፀጥታ ዙሪያ መነጋገራቸውን ጠቁመዋል። በኢትዮጵያ የሶማሊያ አምባሳደር አብዱላሂ ዋርፋ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሶማሊያን ሕዝብ ሰላም እና ፀጥታ ለማረጋገጥ በአሸባሪው የአልሸባብ ታጣቂ ላይ የወሰዳቸውን እርምጃዎች አድንቀው፣ ሠራዊቱ ለሶማሊያ ሕዝብ መስዋዕትነት መክፈሉንም አንስተዋል ተብሏል።

ከዚኹ ጋር በተያያዘ፣ ይኸው የፓርላማው ቡድን፣ አዲስ አበባ በሚገኘው የኢጋድ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመገኘት **በኢትዮጵያ የኢጋድ ተልዕኮ ዋና አሥፈፃሚው አበባው ቢሆነኝ** ጋር፣ የኢጋድ አባል አገራት ፓርላመንተሪ ዲፕሎማሲን በተመለከተ ሰፊ ውይይት ማደረጉም ተጠቀሷል። በውይይቱም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ ሠላም እና ባህልን እንዲኹም የኢጋድ አባል አገራትን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተዳሰዋል ተብሏል። በኢትዮጵያ የኢጋድ ተልዕኮ ዋና አሥፈጻሚው አበባው ቢሆነኝም፣ ኢጋድ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በአባል አገራት መካከል የተከናወኑትን ተግባራት በዝርዝር በመግለፅ፣ ይኽ ተግባር የፐብሊክ ዲፕሎማሲን መሠረት በማድረግ ወደፊትም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አፅንኦት ሰጥተዋል ተብሏል።



*የኢትዮ-ኢጋድ እና የምሥራቅ አፍሪካ አገራት የፓርላማ የዲፕሎማሲ ቡድን አባላት፣ በኢትዮጵያ የኢጋድ ተልዕኮ ዋና አሥፈፃሚው አቶ አበባው ቢሆነኝ ጋር በተወያዩበት ወቅት፤*

**ኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ ያላቸውን የሕግ አውጪዎች የፓርላማ ዲፕሎማሲ** እና ኹለንተናዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል የልምድ ልውውጥ ያካሄዱበት መድረክ ደግሞ፣ የወሩ ኹለተኛው የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን ነበር። እንደራሴዎቹ፣ ከናይጄሪያ የብሔራዊ ጉባኤ አገልግሎት ኮሚሽን የመጣውን ከፍተኛ ልዑክ ተቀብለው ያወያዩ ሲሆን፣ የመድረኩ ዓላማም በዋናነት በእንደራሴዎች ምክር ቤት አወቃቀር፣ ሥልጣን እና ተግባራት እንዲኹም በሕግ አወጣጥ ሂደቶች ዙሪያ ያተኮረ ነበርም ተብሏል።

በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል የአፍሪካ ትልቁ ሀብት መሆኑን አንስተው፣ በወጣቶች ላይ ያተኮሩ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰቶች ለአህጉሪቱ መፃዒ ዕድል ወሳኝ መሆናቸውን መናገራቸው ተጠቅሷል። ከዚኽ ባለፈም፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ አህጉራዊ ፈተናዎችን በጋራ ለመመከት እንደሚያግዝ የገለጹት ሰብሳቢው፣ ኹለቱ አገራት ለዘላቂ ብልጽግና በቅንጅት እንደሚሰሩም አረጋግጠዋል ተብሏል።

የሰው ሀብት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሬ ሌንጮ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ በትምህርት እና ክህሎት ልማት ላይ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች መሆኑን በመጥቀስ፣ ባለፉት ዓመታት በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የገጠመውን ስብራት ለመጠገን እና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል አዲስ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉንም ለልዑኩ ገልጸዋል።

የዚኹ ቋሚ ኮሚቴ አባል የተከበሩ አምባሳደር ዶ.ር. የሺመብራት መርሻ በተራቸው፣ በምክር ቤቱ ውስጥ የሴቶች ውክልና 44 በመቶ መድረሱ እና በሥራ አሥፈጻሚው ውስጥም የአመራርነት ተሳትፏቸው ማደጉ መንግስት ያደረገው መንግስታዊ ማሻሻያ ውጤት መሆኑን ለሉዑኩ ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። የናይጄሪያው ልዑክ መሪ ኮሚሽነር ላዋን ማህሙድ ማና በበኩላቸው፣ የኹለቱን አገራት የፓርላማ ዲፕሎማሲ ግንኙነት ማጠናከር አህጉራዊ ትስስርን ለመፍጠር ያለውን ፋይዳ አብራርተዋል።



*ኹለቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከናይጄሪያ የብሔራዊ ጉባኤ አገልግሎት ኮሚሽን ጋር፤*

በሕግ አወጣጥ እና በሥራ አመራር ሥርዓቶች ዙሪያ የሚደረጉ የልምድ ልውውጦች ጠንካራ እና ዘመናዊ የዴሞክራሲ ተቋማትን ለመገንባት የሚረዱ ቀዳሚ ተግባራት መሆናቸውን ያነሱት ኮሚሽነሩ፣ በኹለቱ አገራት መካከል የሚፈጠር የጠበቀ ትብብር የጋራ

አህጉራዊ ፈተናዎችን ለመፍታት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርም መናገራቸው ተዘግቧል።

**በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መካከል** ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተነገረበት ኹነትም፣ የወሩ ሌላይኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የኢትዮ-ኢጋድ እና ምሥራቅ አፍሪካ አገራት የፓርላማ ዲፕሎማሲ ቡድን አባላት፣ አዲስ አበባ በሚገኘው የጅቡቲ ኢምባሲ በመገኘት ከአምባሳደሩ ተወካይ እና ከጅቡቲ ዲፕሎማቶች ጋር በኹለቱ አገራት መካከል ስላለው የፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ ሠላም እና ባህል በተመለከተ እንዲኹም የኢትዮ-ጂቡቲ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እና ፓርላመንታሪ ዲፕሎማሲን በማጠናከር ዙሪያ ሰፊ ውይይት አድርገዋል ተብሏል።

የቡድኑ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ መስፍን እርካቤ፣ የኹለቱን አገሮች የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ግንኙነት እና ትብብርን አሥመልክቶ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ምክትል ሰብሳቢው በዚያ ማብራሪያቸው፣ በተለይ ኢትዮጵያ ለጅቡቲ ሕዝብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ የንጹሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ አትክልት እና ፍራፍሬ የመሳሰሉትን ምርቶች እንደምታቀርብ እና ከኹሉም በላይ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ አገራቱን ያስተሳሰረው የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት ግንኙነት ዋንኛ መገለጫ መሆኑን አንስተዋል ተብሏል። በጅቡቲ ኢምባሲ በኩል የአምባሳደሩ ተወካይ ሞሀመድ አብዲ እና ኦስማን አሊ እንዲኹም አሚና ሙሳ፣ ኢትዮጵያ የጅቡቲ አጋር እና ወዳጅ አገር መሆኗን መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷቸዋል።




*የኢትዮ-ኢጋድ እና ምሥራቅ አፍሪካ አገራት የፓርላማ ዲፕሎማሲ ቡድን፣ ከጅቡቲ አምባሳደር ተወካይ እና ከጅቡቲ ዲፕሎማቶች ጋር፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ **የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በኢትዮጵያ የደቡብ አፍሪካ አምባሳደር ጋር** በኹለቱ አገራት የኹለትዮሽ ግንኙነት ዙሪያ የተወያየበት ኹነት ደግሞ፣ የወሩ የምክር ቤቱ የመጨረሻው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ የምትከተለው ፓርላመንታዊ የዲሞክራሲ ሥርዓት መሆኑን እና የእንደራሴዎቹ ምክር ቤትም ጠቅላይ ሚኒስትር የመሰየም እና የሚኒስትሮችን ሹመት የማፅደቅ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ወሳኝ ተቋም መሆኑን አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ታዳጊ ዲሞክራሲ ካላቸው አገራት መካከል እንደ መሆኗ ይኽንኑ ሥርዓት ይበልጥ አጠናክራ እንደምትቀጥል የተናገሩት ሰብሳቢው፣ ደቡብ አፍሪካም ተመሳሳይ ፓርላማንታዊ ዲሞክራሲ የምትከተል እና ፕሬዝዳንቷን የምትመርጥበት ሥርዓት በመሆኑ፣ በፓርላማ ዲፕሎማሲ የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንደሚቻል ጠቁመዋል ተብሏል።

የደቡብ አፍሪካው አምባሳደር ኖንሴባ ሎሲ በበኩላቸው፣ የአገራቱ ልዩ ታሪካዊ ግንኙነት ከኔልሰን ማንዴላ ዘመን እና ከፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ጀምሮ ጠንካራ መሰረት ያለው መሆኑን አስታውሰው፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ከማሳደግ ባለፈ የፓርላማ ዲፕሎማሲን ይበልጥ ለማጠናከር እና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እንደሚሰሩም አረጋግጠዋል ተብሏል።



***የደቡብ አፍሪካ አምባሳደሯ እና የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፤***

## 4. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ባሳለፍነው ሚያዚያ ወር፣ **የምክር ቤታቸውን ጽሕፈት ቤት የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም** መገምገማቸው፣ የወሩ ዋንኛ የ'ራስ በ'ራስ ክውናቸው ነበር። ሪፖርቱን ያቀረቡት የጽሕፈት ቤቱ ዋና ጸሓፊ ተወካይ ከረዩ ባናታ ሲሆኑ፤ ውጤታማ የፓርላማ አገልግሎት አሰጣጥን እውን ለማድረግ ጽሕፈት ቤቱ ዕቅድ ማዕከል ያደረገ ተጨባጭ ለውጥ አምጪ ተግባራትን እያከናወነ እና ክንውኖችን በየጊዜው እየገመገመ እንደሚገኝ ጠቁመዋል ተብሏል።

የጽሕፈት ቤቱ ያለፉት ዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸም፣ በብዙ መልኩ ውጤታማ ነው ሲሉ የተናገሩት ደግሞ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የማሻሻያ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለሠ መና እንደነበሩ ተጠቅሷል። በጽሕፈት ቤቱ በተከናወነው ማሻሻያ መሰረት ተጨማሪ የሰው ኃይል በመቅጠር፣ የጽሕፈት ቤቱን ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ለማጠናከር እየተከናወነ ያለው ሥራ ፋይዳው የጎላ መሆኑን አክለው ያነሱት ሰብሳቢው፣ የኢቲቪ ፓርላማ ቻናልን ለማጠናከር የሚያስችሉ መሟላት የሚገባቸውን ግብዓቶች በወቅቱ ማሟላት፣ ለክፍሉ ባለሙያዎች ሥልጠናዎችን መስጠት ብሎም የቴሌቪዥን ቻናሉ የአመራሩ የተለየ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው አመላክተዋል ተብሏል።

ከዚኽ ባለፈም፣የቀጣይ አምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ከዚህ ዕቅድ ላይ የሚቀዳው የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ አገራዊ ነባራዊ ኹኔታን ባገናዘበ፣ ሳይንሳዊ እና ተቋማዊ ሥራዎችን በምክንያታዊነት ያናበበ ሆኖ በልዩ ትኩረት ሊዘጋጅ እና በጊዜ ሊጠናቀቅ እንደሚገባም ሰብሳቢው አፅንኦት ሰጥተው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

የጽሕፈት ቤቱ ዋና ጸሓፊ ተወካይ ከረዩ ባናታ በበኩላቸው፣ ጽሕፈት ቤቱ ሥራዎችን በዕቅድ በመምራት ኃላፊነትን የመወጣት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን በመጠቆም፤ በተለይ ከግንባታ ጋር የተያያዙ የምክር ቤቱ ሥራዎች ክንውኖቻቸው ውጤታማ እንዲሆኑ በምክር ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ጭምር የቅርብ ክትትል እየተከናወነ መሆኑን አሥረድተዋል ተብሏል።



*የጽሕፈት ቤቱ ዋና ጸሓፊ ተወካይ ከረዩ ባናታ፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

የመንግስት ተጠሪ ጉዳዮች ምክትል ዋና ጸሓፊው አንድነት አድነው በበኩላቸው፣ ጽሕፈት ቤቱ ከማሻሻያው በኋላ የተሻሉ አፈጻጸሞች እንዳሉት

በየጊዜው ከተደረጉ የዕቅድ ግምገማ እና ተጨባጭ አፈጻጸሞች መመልከት ተችሏል ማለታቸው ተጠቅሷል።

## 5. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ባሳለፍነው ሚያዚያ ወር ባካሄደው 17ኛ መደበኛ ስብሰባ **ኹለት ስምምነቶችን** አጽድቋል።

ምክር ቤቱ ባካሄደው 17ኛ መደበኛ ስብሰባው ያጸደቀው ቀዳሚው ስምምነት፣ **በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ** መካከል የተፈረመውን የ80 ሚሊየን ዩሮ የብድር ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ ነበር። ስለ ብድር ስምምነቱ አሥፈላጊነት የተናገሩት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ምሕረቱ ሻንቆ፣ ብድሩ መንግስት የጀመረውን የሀገር በቀል የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድ ለመደገፍ የሚያግዝ የቀላል ብድር ስምምነት መሆኑን ተናግረዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው አክለውም፣ ገንዘቡ መንግስት እያከናወነ ያለውን ሥር-ነቀል የኢኮኖሚ ለውጥ፣ የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ እና የኢነርጂ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችን ለማገዝ የሚውል እና ብድሩ በቀጥታ ወደ መንግስት ግምጃ ቤት የሚፈስ፣ ኹሉን ዓቀፍ የምጣኔ ሀብት ዕድገትን ለማረጋገጥ እና የመንግስትን የበጀት አቅም ለማጠናከር ታስቦ የቀረበ ነው ብለዋል ተብሏል።

የብድር ስምምነቱ የወለድ መጠን በዓመት 1.1 በመቶ ዝቅተኛ ወለድ የሚታሰብበት፣ 0.5 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚፈጸምበት እና የ5 ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ15 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑም ተመላክቷል። እንደራሴዎቹም ስምምነቱን፣ ዐዋጅ ቁጥር 1414/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።

እንደራሴዎቹ በዚኹ መደበኛ ስብሰባቸው ያጸደቁት ሌላኛው ስምምነት፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ማኅበር መካከል** የተፈረመውን የ110 ሚሊዮን ዩሮ የብድር ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ ነበር። ይኽንንም ስምምነት ለእንደራሴዎቹ ያብራሩት ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ምሕረቱ ሻንቆ ሲሆኑ፤ ስምምነቱ በቤተሰብ ደረጃ ገቢን በማሳደግ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን የመቋቋም አቅምን በማሻሻል የኑሮ ኹኔታን ማሻሻል እና ድህነትን መቀነስ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

ብድሩ የሚተገበረው ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በሚገባ በመልሶ ማበደር የብድር ስምምነት መሰረት ባንኮችን፣ ማይክሮ ፋይናንሶችን እና የገጠር ቁጠባ እና ብድር ማኅበራት ዩኒየኖችን በመጠቀም በማኑፋክቸሪንግ፣ በአገልግሎት፣ በንግድ፣ በቱሪዝም እና በግብርና ዘርፎች ለተሰማሩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ለሥራ ፈጣሪዎች የሚቀርብ መሆኑም ተብራርቷል።

ብድሩ በ25 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ፣ በአውሮፓ ኅብረት እና ከግብርና ልማት ፈንድ የተገኘው የእርዳታ ድጋፍ የመልሶ መክፈያን ወጪን በመቀነስ ከኢትዮጵያ የብድር አሥተዳደር ስትራቴጂ ጋር

እንዲጣጣም ተደርጎ የቀረበ ነውም ተብሏል። ምክር ቤቱም፣ የብድር ስምምነት ረቂቅ ዐዋጁን ዐዋጅ ቁጥር 1415/2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።



***እንደራሴዎቹ በረቂቅ ስምምነቶቹ ዙሪያ ሲወያዩ፤***

## 6. ሹመቶች

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሚያዚያ፣ እንደራሴዎቹ ካከናወኗቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶች መካከል ሳይጠቀስ የማያልፈው፣ ለተለያዩ ተቋማት ያጸደቋቸው ሹመቶች ናቸው።

ምክር ቤቱ በወሩ ባካሄደው 16ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ **የተጓደሉ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አመራሮችን ሹመት** መርምሮ አጽድቋል። በዚኽም መሰረት ዶ.ር. ሚዛኔ አባተ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር፣ ወ/ሮ አሸነፈች አበበ የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳዮች ዘርፍ ኮሚሽነር፣ መሃመድ አህመድ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የአካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ጉዳዮች ዘርፍ ኮሚሽነር እንዲኹም በዳሳ ለሜሳ የትምህርት እና ሥልጠና ዘርፍ ኮሚሽነር አድርጎ፣ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ቁጥር 9/2018 አድርጓ ማጽደቁን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በወሩ ባካሄደው ሌላይኛው 18ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ **የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ አመራሮችን ሹመትም** መርምሮ አፅድቋል። ሹመቱን አስመልክቶም፣ በምክር ቤቱ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ምሕረቱ ሻንቆ የውሳኔ ሐሳብ እና ሪፖርት አቅርበዋል ተብሏል። በመጨረሻም፣ እንደራሴዎቹ የሚከተሉትን ተሿሚዎች፣ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ቁጥር 10/2018 አድርገው ሹመቶቹን አፅድቀዋል፤ ተሿሚዎቹም፦

ወ/ሮ ብሌን ማሞ - የቦርድ ሰብሳቢ፣ ክብርት ፈዲላ ቢያ - አባል፣ አቶ ተስፋዬ ዘውዴ - አባል፣ አቶ መሐመድ ካሳ - አባል፣ አቶ አፈወርቅ በደዊ - አባል፣ ወ/ሮ አሥማ ረዲ - አባል፣ አቶ ዮናስ በቀለ - አባል፣ አቶ ሀፍታይ ገ/እግዚአብሔር - አባል እና፣ ዶ.ር. ኢሳይስ ካሳ - አባል መሆናቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።



*ተሿሚዎቹ ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ፤*

## 7. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ በሲቪል ማኅበረሰቡ ከየት ወዴትነት እና ቀጣይ ዕድሎች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሚያዚያ ከከወናቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶች መካከል አንዱ፣ የፌደራል ተቋማትን የዘኽን በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም መገምገም ነበር። ወደ እንደራሴዎቹ አዳራሽ ተጠርተው የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን ካቀረቡት ተቋማት መካከልም፣ **የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን** በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው ነበር።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የተቋሙን ሪፖርት ማድመጡ ሲዘገብ፣ ባለሥልጣኑም፣ በሲቪል ማኅበራት አሠራር፣ የማኅበራት ምዝገባ ሒደት፣ የማኅበራት ገንዘብ አጠቃቀም እና በቀጣዩ ምርጫ ዝግጅት ዙሪያ ያተኮረ ሪፖርት አቅርቧል።

7ኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ተአማኒ እንዲሆን የሲቪል ማኅበራት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፣ በምርጫ ዙሪያ የሚሰሩ ማኅበራትን አቅም የማብቃት ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና ማኅበራቱ በማንኛውም ወገን ተጽዕኖ ሥር ሳይወድቁ ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግም በቋሚ ኮሚቴው በኩል ጠንከር ያለ ትዕዛዝ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ መሰጠቱም ተዘግቧል።

በዚኽ መነሻነትም፣ ተቋማችን ብሪጅ፣ የሲቪል ማኅበረሰቡን ከየት ወዴትነት፣ በሦሥቱ ሥርዓታት ያለፈበትን ጉዞ እንዲኹም አኹናዊ ኹለንተናዊ ገጽታውን አጠር አድርጋ በመዳሰስ፣ ተያያዥ ተቋማዊ ምክረ-ሐሳቦችንም ለመሰንዘር ይኽችን ሳምንታዊ ዳሰሳ እነሆ ትላለች።

### 7.1. ሲቪል ማኅበረሰብ ሲሉ...

ሲቪል ማኅበረሰብ ማለት ምንድን ነው? ለሚለው የሚቀርበው ብያኔ በከፊልም ቢሆን ልዩነቶች ይታዩበታል። በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚናም የተለያዩ የሐሳብ ጫፎች ሲነገሩ ይስተዋላል። እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ሲቪል ማኅበረሰብ ማለት፣ ለመንግሥታት በተለዋጭነት የሚውል ንባበ-ቃል ነበር። ከበኩር አሳቢዎች መካከል ቀዳሚው የሆነው ጀርመናዊው ፍሬዴሪክ ሄግል፣ በሲቪል ማኅበረሰብ እና በመንግሥት መካከል ልዩነት መኖር እንዳለበት በመከራከር የመጀመሪያው ጸሐፊ ነው። ለ'ርሱ ሲቪል ማኅበረሰብ ማለት በቤተሰብ እና በመንግሥት መካከል የሚቆም፣ በፖለቲካ ማኅበረሰቡ የተገፉ ዜጎች ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር እና እውቅና ለማግኘት በሚል የሚፈጥሩት ተቋም ነው።

በብላቴናነቱ ዘመን ሄግል ያደላለት እና ክስተቶችን በሙሉ ከመደብ ትግል አንጻር ለሚያየው ካርል ማርክስ የሄግል ብያኔ የሚስማማው ቢመስልም፣ እንደሌላው ኹኔታ ኹሉ ሲቪል ማኅበረሰቡም የግለሰባዊ ፍላጎቶች እና የመደብ ጥያቄ ትግል የሚያካሂዱበት መድረክ እና

የትግሉ ውጤትም ማዕከላዊ መንግሥቱን በአብዮት ለመጣል ድርሻ እንዳለው አድርጎ ያቀርበዋል።

ከማርክስ፣ “መንግሥትን ከማኅበረሰቡ ስናወጣው” ከሚለው የሲቪል ማኅበረሰብ ትርጓሜ ይልቅ፣ የጣሊያናዊው ማርክሲስት አንቶኒዮ ግራምሺ ዕይታ የተሻለ ነው ተብሎ ይታመናል። በግራምሺ ዕይታ መሰረት ዜጎች በቤተ-እምነቶቻቸው፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሙያ ማኅበራት እና የትምህርት ተቋማት በኩል ራሳቸውን እና ሐሳባቸውን የሚወክሉባቸው ተቋማት ስብስብ ሲቪል ማኅበረሰብ ተብሎ መጠራት እንዳለበት ‘የእስር ቤት ማስታወሻዎች’ በሚለው ስብስብ ድርሳኑ ጽፏል።

ምንም እንኳን በምሁራን እና በሲቪል ማኅበረሰብ ተዋናዮች መካከል ብያኔውን በተመለከተ ምን ዓይነት መስፈርቶችን መጠቀም አለብን የሚለው የልዩነታቸው ምንጭ ቢሆንም፣ አስማሚ የሚመስለው ሐሳብ፣ በዜጎች ሙሉ ፈቃደኝነት ከመንግስት እና ትርፍን ከማግኘት ውጪ የሚደራጁ ተቋማት በዚኽ ስም ሊጠሩ ይችላሉ የሚለው ምልከታ ነው። የሚመሰርቷቸውን ዜጎች ፍላጎቶች የተለያዩ ሕጋዊ መንገዶችን በመጠቀም ለመፈጸም የሚተጉ፣ መንግስት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የሚሹ፣ በማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ በፖለቲካ ምኅዳር መስፋፋት እና በዲሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ ላይ አዎንታዊ ጫና ለማድረግ የሚችሉ የተለያዩ ሀገር-በቀል አልያም በሌሎች ደጋፊነት የሚንቀሳቀሱ ተቋማት በዚኽ ብያኔ ውስጥ ያርፋሉ።

በዲሞክራሲ ሂደት መፋጠን እና በሲቪል ማኅበረሰብ ሚና ላይ የሚጽፉ ምሁራን፣ በኹለቱ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ዝምድና እንዳለ ይከራከራሉ። ጠንካራ የሲቪል ማኅበረሰብ የሐሳብ ብዝሓነትን በማስፋፋት የዲሞክራሲ እሴቶች በአገሪቱ ተቋማት ውስጥ እንዲሰርጹ ማድረግ የሚያስችል አቅም ይኖረዋል። ድምፃቸው የታፈነ እና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ጥግ የተገፉትን የማኅበረሰብ ክፍሎች በመወከል ማኅበራዊ ፍትሕን ለማምጣትም በጎ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ። የፖለቲካ ሥርዓቱም ቢሆን ባወጣቸው ሕግጋት መጠን ልክ ሲቆጣጠሩ፣ የሙስና መስፋፋትን ሲገቱ፣ በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚካሄዱ ውሳኔዎች ግልፅነት እንዲኖራቸው ሲያነሳሱ፣ የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያሳድጉበትን ኹኔታዎች ሊያመቻቹ የሚችሉ ተቋማዊ ባህሪያት አሏቸው። በብዙ ጸሐፊዎች መካከልም እነዚኽ ተግባራት የሚከናወኑ ተቋማት መብዛት የዲሞክራሲያዊ ሂደቶችን መጠናከር ሲያመለክቱ፣ በተቃራኒው የድርጅቶቹ መዳከም የአምባገነናዊ የፖለቲካ ሥርዓትን ስር መስደድ መሆኑን ቢያነስ ያለፉት ሦሥት ዓሥርታት በበቂ የሚያሳዩት ሃቅ ነው።

## 7.2. የአጼው ዘመነ-መንግሥት

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት የነበረው የሲቪል ማኅበረሰብ እንቅስቃሴ፣ ከባሕላዊ እና ማኅበረሰብ-ተኮር የራስ-አገዝ ማኅበራት ወደ ዘመናዊ እና መደበኛ ማኅበራት የተሸጋገረበት ወቅት ነበር። ይኹን እንጂ አጠቃላይ ምኅዳሩ በንጉሠ ነገሥቱ መዳፍ ሥር

የወደቀ እና ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት እንደነበር ብዙ ተጽፎበታል።

ለዘመናት ኢትዮጵያ ጠንካራ ባሕላዊ የሲቪክ ተቋማትን ጠብቃ የቆየች ሲሆን፣ ከእነዚኽም መካከል ዕድር፣ ዕቁብ እና ደቦ ተጠቃሾች ናቸው። በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ግን የሠራተኛ ማኅበራት፣ ሌሎች የሙያ ማኅበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ጨምሮ ዘመናዊ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። እነዚኽ መደበኛ ድርጅቶች በዐዋጅ ቁጥር 321/1959 መሠረት በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር ይመዘገቡም ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱ የዘመናዊነት እና የትምህርት መስፋፋት ፖሊሲ፣ ለሲቪል ማኅበራት መፈጠር መሠረት የሆነውን የተማረ የሰው ኃይል እና መካከለኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ለመፍጠር ረድቷል። በእነዚኽ የዘመኑ ምሁራን ዘንድም የጃፓንን ፈለግ በመከተል የታመነ እና አገሪቱን ለማዘመን የሚተጋ እንቅስቃሴ ተፈጥሮ ነበር። በዘመነ-መንግሥቱ ማብቂያ ላይ ግን የመሬት ይዞታ ማሻሻያ እና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሚወተውት ሥር-ነቀል የተማሪዎች ንቅናቄ ብቅ ብሎ የነበረ ሲሆን፤ ይኽም ሥርዓቱን በግልጽ የሚቃወም ነበር። በተጨማሪም በ1966 ዓ.ም የተከሰተው ድርቅ እና ችጋር፣ የመንግሥትን ድክመት ከማጋለጡ ባለፈ፣ እንደ የክርስቲያን ረድኤት እና ልማት ማኅበር ያሉ ቀደምት የረድኤት ድርጅቶች እንዲመሰረቱ ምክንያት ሆኗል።

ምንም እንኳ በዚኽ መልኩ ዘመናዊ የሲቪል ማኅበራት ቢፈጠሩም፣ መንግሥት ጥብቅ ክትትል ያደርግባቸው ስለነበር በነፃነት የመንቀሳቀስ ዕድላቸው ውስን ነበር። የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ግልጽ ተቃውሞዎች ይታገዱ እንደነበረው ኹሉ፣ ሌሎቹም ተቋማዊ ለመሆን ይጥሩ የነበሩ ሀገር በቀል የሲቪል ማኅበራትም ዕጣቸው እንዲያው ሆነ። እነዚያ ብቅ ያሉት የሲቪል ማኅበረሰብ መዋቅሮችም ቢሆኑ፣ በብዛት ተጠቃሚ ያደረጉት ከተሜውን እንጂ ገበሬውን አልነበረም። ይኽ በንጉሡ ዘመን የተጀመረው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንቅስቃሴ፣ ከ1966ቱ አብዮት በኋላ በመጣው የደርግ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተቀይሮ፣ ገለልተኛ ማኅበራት በመንግሥት በሚመሩ የሕዝብ ድርጅቶች እንዲተኩ ተደርጓል።

## 7.3. ጸረ-ሲቪል ማኅበረሰቡ ደርግ

ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም ኢትዮጵያን የገዛው ደርግ፣ በሰፊ የፖለቲካ ጭቆና እና በሲቪል ማኅበረሰቡ ላይ በተጣለ ጥብቅ ቁጥጥር የሚታወቅ ነበር። በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይመራ የነበረው ወታደራዊው መንግሥት፣ በግራ ዘመም መርሆዎች ላይ የተመሠረተ የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለምን ተግባራዊ ማድረጉ ይታወሳል። ሥርዓቱ መሬትን እና ኢንዱስትሪዎችን ወደ መንግሥት ይዞታ በማዛወር ኢኮኖሚያዊ ርዕታዊነት ያለው ማኅበረሰብ ለመፍጠር ቢመኝም፣ ፖሊሲዎቹ ግን ለኢኮኖሚ ውድቀት፣ ለምግብ እጥረት እና ለከፋ

ድህነት ዳርገዋል። ይኽም በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታን እና ኋላም የትጥቅ ትግልን ቀስቅሷል።

በዚኽ ዘመን የነበረው የሲቪል ማኅበረሰቡ እንቅስቃሴ ከመንግሥት በደረሰበት ከፍተኛ አገዳ እና አፈና ምክንያት ሽባ ሆኖ ነበር። ደርግ፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በማገድ በሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ በሚዲያ እና በተቃዋሚ ድምፆች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ጥሏል። የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በስፋት ይፈጸሙ የነበረም ሲሆን፣ የሥርዓቱ ተቃዋሚ ናቸው ተብለው በሚጠረጠሩ ዜጎች ላይ ድብደባ፣ ያለ ፍርድ ግድያ እና አስገዳጅ ስወራዎች ይፈጸሙባቸው ነበር።

በንጉሡ ዘመን የነበሩ እንደ ተማሪዎች ቡድን፣ የሠራተኛ ማኅበራት እና የሃይማኖት ድርጅቶች ያሉ ንቁ የሲቪል ማኅበረሰብ ተዋናዮች ከፍተኛ ስደት እና ስቃይ ደርሶባቸዋል። በርካታ የሲቪክ መሪዎች ታስረዋል፤ ተገድለዋል ወይም አገር ጥለው እንዲሰደዱ ተገድደዋል። ይኽ አፈና የሲቪል ማኅበረሰቡን አቅም በማዳከሙ፣ ሥርዓቱን በሰላማዊ መንገድ መሞገት የማይቻልበት ደረጃ ላይ አደረሰው። ይኽ የጭቆና ዘመን በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ትስስር ላይ የከፋ ጠባሳ ጥሎ ከማለፉ ባለፈ፣ ሥርዓቱ ከወደቀ በኋላም ለረጅም ጊዜ የዘለቀ የፍርሃት እና የመተማመን እጥረት እንዲሰፍን አድርጓል።

ደርግ ገለልተኛ የሲቪል ማኅበራትን በማፍረስ፣ በእነሱ ምትክ በመንግሥት እና በፓርቲው (ኢሠፓ) የሚመሩ የጅምላ ማኅበራትን አቋቁሟል። ከእነዚኽ መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉት አብዮታዊ የኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር (አኢወማ)፣ አብዮታዊ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር (አኢሴማ) እና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር (ኢሠማ) ናቸው።

ነገር ግን የእነዚኽ ድርጅቶች ምሥረታ ያስፈለገው የዜጎችን ፍላጎት ለማንፀባረቅ ሳይሆን፣ ማኅበረሰቡን ለመቆጣጠር፣ ወታደራዊ ቅስቀሳ ለማድረግ እና የመንግሥትን ፖሊሲዎች ለማስፈጸም በተቀጥላነት እንዲያገለግሉ ነበር፤ አባልነት እንኳ በግዴታ መሆኑን ያስታውሷል። በዚኽ መልኩም፣ ንጉሡ ሳይነኳቸው የቆዩት እንደ ዕድር ያሉ ባሕላዊ ተቋማት ሳይቀሩ በደርግ ዘመን ለፖለቲካዊ ዓላማ እንዲውሉ ተደርገዋል። ዕድሮች ከመቃብር እና ከማኅበራዊ ድጋፍ ባለፈ፣ የመንግሥት መልዕክት ማስተላለፊያ እና አልፎ ተርፎም ተቃዋሚዎችን መከታተያ እንዲሆኑ ጫና ይደረግባቸው ነበር።

በደርግ ዘመን ብቸኛው ነፃ ሊባል የሚችል የሲቪል ማኅበረሰብ እንቅስቃሴ የታየው በሰብዓዊ እርዳታው ዘርፍ ነበር። በተለይ በ1977ቱ አስከፊ ችጋር ወቅት፣ መንግሥት ዓለም ዓቀፍ ዕርዳታን ለመቀበል በመገደዱ፣ በርካታ ዓለም ዓቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቅዷል። ይኽም ዘመናዊው እና በዕርዳታ ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ታሪክ መሠረት እንዲጣል አድርጓል። ሆኖም እንቅስቃሴያቸው በረሃብ እና በምግብ ድጋፍ ላይ የተገደበ እንጂ በፖለቲካ እና በሰብዓዊ መብቶች ላይ እንዳይሳተፉ ጥብቅ ገደብ

መጣሉ፣ ኢትዮጵያ ልታገኝ ትችል የነበረውን የዘመናዊ ሲቪል ማኅበረሰብ ዕድገት ቀጭቶታል።

## 7.4. የኢሕአዴግ ሦሥቱ ምዕራፎች

የቀዝቃዛውን ጦርነት ማብቃት ተከትሎ፣ ሉላዊው ዓለም ከሊበራል ዕሴቶች ውጪ የመመልከት ዕድል ለማጣት ተገደደ። በዚኽ የተነሳም፣ በዚያ ዘመን ወደ ሥልጣን የመጡ ገዚዎች፣ የሊበራል ፖለቲካ ሥርዓት መንበር አንዱ አምድ የሆነውን የሲቪል ማኅበራት ሚናን ለመቀበል ተገደዱ። በኢትዮጵያም የሆነው እንዲኹ ነበር፤ በደርግ መውደቅ ማግስት ወደ መንበሩ የመጣው ኢሕአዴግ፣ የሲቪል ማህበራትን ዲሞክራሲያዊ ሚና ከመቀበል ውጪ፣ ዘመኑ ሌላ አማራጭ አልሰጠውም። በዋናነት በዚኽ ውጪያዊ ግፊት የተነሳ፣ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ታሪክ ውስጥ በበጎ የሚነሳው ዘመን አሀዱ አለ። ከዚኽ አኳያም፣ የዚኽን ዘመን የተለያዩ ገጾች ሰፋ አድርጎ መመልከት፣ ለጥቆ ለመጣው ላለንበት ዘመን ሰፋ ያለ ስዕል ሳይሰጠን አይቀርም።

ኢሕአዴግ ከሲቪል ማኅበረሰቡ ጋር የነበረው የግንኙነት ተዛምዶም ሦሥት ምዕራፎች እንዳሉት ርዕሰ-ጉዳዩን ያጠኑ ተንታኞች ይሚገታሉ። የመጀመሪያውን ደመናዊ ጥላቻ ያረበበት ዘመን ሲሉ የሚጠሩት እነኚ ጸሓፍት፣ እስከ 1993ቱ የኢትዮ-ኤርትራው ጦርነት መጀመሪያ ድረስ የቀጠለውን ይኽን የኹለቱ የግንባሩን እና የሲቪል ማኅበረሰቡን ሒደት ይጠቀልላል። ይኽም ፓርቲው ከትጥቅ ትግል ታሪኩ ካሳየው ባህሪ ጋር እንደሚቆራኝ ይጠቅሳሉ። እንደ ጉሬላ ታጣቂ ቡድን እና ርዕዮተ-ዓለሙን በግራ-ዘመም አስተምህሮት እንደቃኘ ግንባር፣ ነፃ የሆኑ ተቋማትን የሚያያቸው በከፍተኛ ጥርጣሬ ነበር። ሥልጣን ከያዘ በኋላ በተከተሉት ዓመታትም ቢሆን፣ ከዚህ የጥርጣሬ መንፈሱ አልተላቀቀም። አንዳንዶቹ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለፓርቲው ድጋፍ ሲሰጡ የቆዩ ቢሆኑም፣ እርሱ ከሚቆጣጠራቸው ማኅበራት ውጪ ያሉትን ድርጅቶች ሥልጣኑን እንደሚቀናቀኑ ኃይሎች ማየቱ በጊዜው ለነበሩት የመያዶች ቁጥር መቀነስ አንደኛው ምክንያት ነበር። ይኽ የፓርቲው የተጠራጣሪነት አካሄድም ይመስላል፤ እንደሌሎቹ የአፍሪካ አገራት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ በኋላ የመያዶች ቁጥር መጨመር በኢትዮጵያ የተከሰተበት ዕድል እንዲጠብ ያደረገው የሚለው አንዱ በዛ ብሎ የሚጠቀስ የክርክር ነጥብ ነው።

አጥኚዎቹ የሚያነሱት ኹለተኛው ምዕራፍ፣ ጸሓፍቱ ዝግ ብለው የሰየሙት ሲሆን፣ ይኽም ከ1980ዎቹ መጨረሻ እስከ ድህረ-97 ምርጫ ድረስ የሚዘልቀውን ዘመን ያቅፋል። ጸሐፍቱ ዝግ ብለው በሰየሙት በዚኽ ምዕራፍ፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ ከመንግሥት ጋር የነበረው መስተጋብር ሦሥት መሠረታዊ መልኮችን ይዞ ታይቷል።

የመጀመሪያው መልክ፣ የድርጅቶቹ ቁጥር መጨመር እና የተሰማሩበት ዘርፍ ብዝኃነት ነው። በዚኽ ወቅት መያዶች ከተለመዱት የረድኤት እና የልማት ሥራ ወጥተው፣ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ፣ በዲሞክራሲያዊ ግንባታ እና በመልካም አሥተዳደር ዙሪያ በስፋት ወደ

ሕዝባዊ አደባባዩ መውጣት የጀመሩበት ነበር። ይኽም ሲቪል ማኅበረሰቡ እንደ አንድ ገለልተኛ ሥርዓታዊ ተዋናይ እና የለውጥ ኃይል ዕውቅና ማግኘት እንዲጀምር መንገድ ከፍቷል።

ኹለተኛው መልክ፣ በፖሊሲ ቀረጻ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የተስተዋለው የተሳትፎ ዝንባሌ ነው። መንግሥት በዚኽ ወቅት እንደ ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ባሉ አገራዊ ፖሊሲዎች ላይ የሲቪል ማኅበረሰቡን ድምፅ እና ግብዓት ለማካተት በማዕከላዊ መንግስቱ በኩል ከፍተኛ ፍላጎት መታየቱ ተስተውሏል። ይኽም ድርጅቶቹ ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ቅርበት በመጠቀም የመንግስትን የልማት አቅጣጫዎች እንዲሞግቱ እና አማራጭ ሐሳቦችን እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጥቷቸዋል። ይኽም በኹለቱ አካላት መካከል የነበረውን የቆየ ጥርጣሬ በማርገብ፣ ወደ መደበኛ የምክክር ባህል የመሸጋገር ተስፋን አጭሮ ነበር።

ሦሥተኛው የዚኽ ምዕራፍ መልክ ደግሞ በሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት እና በሲቪል ማኅበረሰቡ ተወካዮች መካከል የተፈጠረው መዋቅራዊ ትስስር ነው። በዚኽ ወቅት በምክር ቤቱ አባላት እና በመያዶች መካከል መደበኛ የግንኙነት ስምምነት ተደርጎ የነበረ ሲሆን፣ ይኽም ሲቪል ማኅበራት በምክር ቤቱ የሕግ ማርቀቅ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ እና በቋሚ ኮሚቴዎች በኩል የሙያ ድጋፍ እንዲሰጡ የሚያስችል ነበር። ምንም እንኳ ይህ ግንኙነት በ1997ቱ ምርጫ ማግስት ቢቋረጥም፣ ለጥቂት መያዶች ግን መንግስትን የመወትወት እና በሕግ አወጣጥ ሂደት ላይ ተፅዕኖ የማሳደር ኋላ ያልተደገመ ታሪካዊ ዕድል ፈጥሮላቸው ነበር።

ገዢው ፓርቲ ከድህረ-97 ምርጫ በኋላ የተከሰተውን የአገሪቱን የፖለቲካ ሥርዓት የገመገመበትን እይታ መመልከትም ግድ ይላል። ይኽ ሦሥተኛው ምዕራፍ ተብሎ የተጠራው ዘመን፣ በራሱ በፓርቲው መልካም ፈቃድ መራጮችን በማስተማር ምርጫውን በመገምገም ላይ የተሰማሩትን መያዶች፣ የገመተውን የምርጫ ውጤት ካጣ በኋላ ከክስተቱ፣ ‘ድርጅቶቹ ከተቃዋሚዎች ጋር ሰርተዋል’ የሚል እምነት እንዲወስድ አድርጎታል። በ1999 ዓ.ም. “ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚደረግ ትግል” በሚል ርዕስ ፓርቲው ያሳተመው ድርሰትም መያዶችን እንዴት ይመለከታቸው እንደነበር ከፊል እይታ ይሰጣል። ብዙ ተንታኞች፣ ምክንያታዊነት የሌለው ባዶ ሃቲት ሲሉ በጠሩት በዚኽ ጹሑፍ፣ ፓርቲው ስለ “ኪራይ ሰብሳቢነት” ይተነትናል፤ እንደ ፓርቲው ሙግት ሥልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል እና ተቋማዊ ገቢን እርሱ “ልማታዊ ያልሆኑ” ላላቸው ጉዳዮች ማዋል የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫዎች ሆነው ቀረቡ። ከ“ኪራይ ሰብሳቢ” መንግስታት የሚመጡ የገንዘብ ምንጮችን የሚጠቅመው አልያም የድርጅቶቹን የበላይ አመራሮች ጥቅሞች ብቻ ለማስጠበቅ የቆሙ ናቸው ሲል መያዶችን የሚከሰው ይኸው ሰነድ፣ ተቋማቱ በተፈጥሯቸው ጭምር “ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው” ሲል ይራገማል።

ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም ውጭ ያሉ የሐሳብ ሥርዓቶች ለአገሪቱ ልማትም ሆነ ለዲሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ የሚረባ አበርክቶ እንደማይኖራቸው ያመነው ገዢው ፓርቲ፣ በመልካም አስተዳደር፣ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ እና አማራጭ የፖሊሲ ሐሳቦችን በማቅረብ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን፣ የፓርቲውን ኹሉ ቦታ የመኖር እና ኹሉን የመቆጣጠር ህልም እንደሚገዳደሩ ክፍሎች በማየቱ፣ በድህረ-97 ምርጫ የሕገ-መንግስቱን መንፈስ የሚንዱ ሕግጋትን እንዲያወጣ አስገደደው።

በአጭሩ ለማስቀመጥም፣ ፓርቲው ሲቪል ማኅበራትን የተረዳቸው የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ልዕልና ለማስጠበቅ ለሚያስችል የፖለቲካ ማስጠመቂያ እና ለፕሮፓጋንዳ መዋያ ሊሆኑ ይገባል በሚል ነበር። ከዚኽ ዕይታው ውጪ፣ ለተመሰረቱበት ተቋማዊ ርዕይ የተገዙ ሲቪል ማኅበራትን፣ አንድም በአፋኝ ሕግጋት፣ አንድም በፖለቲካ እና የጸጥታ መዋቅር ከሕዝባዊ አደባባዩ እንዲከስሙ አደረጋቸው። ብዙዎች ነገረ-ጉዳዩን ያጠኑ እንደሚጠቅሱት፣ ኹላ በ2010 ዓ.ም የመጣውን የሥርዓት ለውጥ ካዋለዱ ኩነቶች አንዱ፣ ተስፋ ሰጪ የነበረው የሲቪል ማኅበረሰቡ የዕድገት ሂደት በዚኽ መልኩ መጨፍለቁ፣ የተስተዋለውን ሕዝባዊ ዕመጽ እንዲቀሰቀስ ነገሮችን ማመቻቸቱ ነው።

በአጠቃላይ የንጉሠ ነገሥቱ ዘመን፣ የዘመናዊ ሲቪል ማኅበራት መሠረት የተጣለበት እና በመንግሥት መር ዘመናዊነት የተቃኘ ቢሆንም፣ የደርግ ዘመን ግን ሥልጣንን በአንድ ማዕከል የጠፈነገበት እና ገለልተኛ የሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴዎች ጭልጭታን ያጠፋበት የጨላለመ ዘመን ነበር። ከዚያ የቀጠለው እና ብዙ ተስፋ የተጣለበት የድህረ-ደርግ ዘመንም፣ በኢሕአዴግ ኹሉን ጠቅላይነት ናፍቆት ዳሸቀ። ይኽ አጭር የታሪክ ሂደት የሚያሳየው፣ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ዕጣ ፈንታ ምንጊዜም ቢሆን ከፖለቲካዊ ሥርዓቱ ባህሪ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳለው ነው። እነዚኽን ታሪካዊ እውነታዎች መሠረት በማድረግ፣ አኹን ያለውን የብልጽግና ዘመን ምኅዳር በንፅፅር መመልከት ለነገው የዴሞክራሲ ጉዟችን ትልቅ ትምህርት ይሰጣል የሚል ዕምነት አለን።

## 7.5. የባለሥልጣኑ መቋቋም

በደርግ መንግስት መውደቅ ማግስት፣ ከ1983-1987 ዓ.ም. ማኅበራትን የመመዝገብ ሥልጣን እና ተግባር ሲያከናውን የቆየው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰኘው መንግስታዊ ተቋም ሲሆን፤ በ1987 ዓ.ም. አሥፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው ዐዋጅ ቁጥር 4/1987 የኢፌድሪ የፍትኽ ሚኒስቴር የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ አላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና ማህበራትን የመመዝገብ ሥልጣን እና ተግባር በሕግ ተሰጥቶት ነበር፡፡ በቀጣይም በዐዋጅ ቁጥር 471/1998 ይኸው ማኅበራትን እና የሃይማት ድርጅቶችን የመመዝገብ ሥልጣን ለፍትሕ ሚኒስቴር እንደተሠጠ በመቀጠሉ፣ ፍትኽ ሚኒስቴር እስከ 2001

ዓ.ም. ድረስ የመመዝገብ ሥራን ሲያከናውን ሰንብቷል።

የፍትሕ ሚኒስቴር በ1999 ዓ.ም. ባካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት፣ በዘርፉ የተመዘገበውን ዕድገት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከሃይማኖት ድርጅቶች ውጭ ያሉ ማኅበራትን እና ዓላማቸው ለትርፍ ያልሆኑ ድርጅቶችን የመመዝገብ እና ለማሥተዳደር ያስችል ዘንድ፣ በዐዋጅ ቁጥር 621/2001 "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ" በሚል ስያሜ ራሱን የቻለ የመንግስት አሥፈጻሚ አካል እንዲቋቋም ተደርጓል።

በዐዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ተደራጅተው በአገሪቱ ኹለንተናዊ ዕድገት፣ ልማት እና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ በመመዝገብ እና ፈቃድ በመስጠት እንዲኹም በመከታተል እና በመደገፍ የኅብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚል ተልዕኮ ይዞ ቢንቀሳቀስም የመደራጀትን መብት በተሟላ ሁኔታ ያላከበረ እና በአፈፃፀሙም በርካታ ክፍተቶች የነበረበት ስለነበረ ተልእኮውን በተገቢው የተወጣ አልነበረም የሚል ግምት በመንግስት በኩል ተይዞ ሰንብቷል።

በተለይም ዐዋጁ የድርጅቶች እና የማኅበራት የእንቅስቃሴ አድማስ እና የገቢ ምንጭ ላይ ገደብ በመጣሉ የተነሳ ከፍተኛ ቅሬታ ሲቀርብበት የነበረ ዐዋጅ ነበር። በመሆኑም በአገር ዓቀፍ ደረጃ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ ዘርፉን የሚያስተዳድረው ዐዋጅ እና አፈጻመሙ ክፍተት እንዳለበት ስለታመነ ዐዋጅ ቁጥር 621/2001 ሙሉ በሙሉ ተሽሮ በአዲስ ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 ሊተካ ችሏል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱም፣ በዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ ዳግም ተደራጅቶ እንዲቋቋም ሆኗል።

## 7.6. ተስፋው በናልን?

የብልጽግና ፓርቲ ወደ ሥልጣን መምጣት በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ምኅዳር ላይ የታሪክ ሽግግር ያመጣ ክስተት ነበር። መንግሥት መጀመሪያ ላይ ያከናወናቸው የሕግ ማሻሻያዎች እና የዴሞክራሲ ተስፋዎች፣ በዘርፉ ተዋናዮች ዘንድ ከመንግሥት ጋር በቅርበት ለመሥራት እና ሰፊ ለውጦችን ለማምጣት ትልቅ መነቃቃትን ፈጥረው ነበር። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶችን በማስፋፋት፣ ለሰብዓዊ መብቶች በመሟገት እና ለተገለሉ ማኅበረሰቦች መሠረታዊ አገልግሎቶችን በመስጠት ረገድ ጠቃሚ ሚናዎችን መጫወት ጀመሩ።

በተለይም በ2011 ዓ.ም. የወጣው ዐዋጅ (ቁጥር 1113/2011) በውጭ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጥሎ የነበረውን ገደብ በማንሳቱ፣ በሰብዓዊ መብት እና በሰላም ግንባታ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ዳግም እንዲያንሰራሩ አድርጓል። በዚኽም በ2011 እና 2014 ዓ.ም. መካከል ብቻ 250 የሚጠጉ አዳዲስ

የሰላም ግንባታ ድርጅቶች ተመስርተው ለዴሞክራሲ ግንባታው አጋርነታቸውን አሳይተዋል።

በአሁኑ ወቅት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ከተመዘገቡት 4938 ድርጅቶች ውስጥ ከ4395 በላይ የሚሆኑት ሀገር በቀል ድርጅቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ከ543 በላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ደግሞ የውጪ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ከ415 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተለያዩ ሙያዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ የሙያ ማህበራት ሲሆኑ፤ ከ165 በላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አካል ጉዳተኞችን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ድርጅቶች መሆናቸውን የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ድረ-ገጽ ይጠቁማል። እነዚኽ ድርጅቶች ከሀገር በቀል ጥቃቅን ማኅበራት እስከ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት የሚዘልቁ ሲሆን፣ ይኽም በሲቪል ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከታችኛው የማኅበረሰብ ክፍል ጀምሮ እስከ ሰፊው ዓለም ዓቀፍ ትብብር ድረስ ያሉ ልዩ ልዩ የሥራ አቀራረቦችን መኖራቸውን ያሳያል።

በተጨማሪም፣ በርካታ በሰብዓዊ መብት እና በልማት ላይ ያተኮሩ ድርጅቶች እንዲሁም በሴቶች ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ድርጅቶች በመረጡት የሲቪል ማኅበረሰብ ሥራዎች ላይ ተሰማርተዋል። እነዚኽ ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ ከግጭቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የሥርዓተ-ጾታ እና የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን እንደሚዳስሱም ብሪጅ ባደረገችው አጭር ዳሰሳ መረዳት ችላለች። ይኽም የሰላም ግንባታ ሥራ ግጭቶችን ከመከላከል ባለፈ የሰብዓዊ መብቶችን ማስከበርን እና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥን የሚያካትት ኹለንተናዊ ተግባር መሆኑን ያሳያል።

## 7.7. ከተቋሙ ሪፖርቶች ጥቂት ነጥቦች

በመግቢያችን እንደጠቀስነው፣ ለዚኽ ዳሰሳ መነሻ የሆነን የኢፌድሪ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን የዚኽ በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ነውና፣ ከዚኹ የተቋሙ ሪፖርት አንኳር ነጥቦችን መመልከት ፋይዳ ይኖረዋል። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የምዝገባ ፈቃድ የሚያገኙት፣ ጥያቄያቸው ከአገር ደኅንነት አኳያ ተመርምሮ መሆኑን ባለሥልጣኑ መናገሩ ተዘግቧል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ፣ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክቱ ድርጅቶችን ጉዳይ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ጋር በመሆን፣ በተለይም ከአገር ደኅንነት አንጻር በጥንቃቄ ከተመለከተ በኋላ ፈቃድ እንደሚሰጥ አስታውቋል።

የዘጠኝ ወራት የአፈጻጸም ሪፖርቱን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ያቀረቡት የባለሥልጣኑ የስትራቴጂ ጉዳዮች መሪ ሥራ አሥፈጻሚ ወይዘሮ ቃልኪዳን መንግሥቴ፣ ድርጅቶች አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው እስከቀረቡ ድረስ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል ተብሏል። በዚኽም መሠረት ባለፉት ዘጠኝ ወራት 209 ድርጅቶች የዕውቅና ምስክር ወረቀት ያገኙ ሲሆን፣ ከእነዚኽ መካከል 199 የሚሆኑት የውጭ ድርጅቶች መሆናቸው ታውቋል። ከዚኽም በተጨማሪ አዲሱ ዐዋጅ ከወጣ

በኋላ ደግሞ ያልተመዘገቡ እና አድራሻቸው ያልታወቁ 600 የሚጠጉ ድርጅቶች መኖራቸውን የጠቀሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፋሲኮ ሞላ ተናግረዋል፤ እነዚኽ ድርጅቶችም ሕጋዊ ሰውነታቸውን እንዲያጡ መደረጉም ተጠቁሟል። ከእነዚኽ ድርጅቶች መካከል የተገኘ ጥቂት ሀብትም በሕጉ መሠረት ወደ ሌሎች ድርጅቶች ወይም ወደ ሲቪል ሶሳይቲ ፈንድ ገቢ እንዲሆን መደረጉም ተብራርቷል።



***የኢፌድሪ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን ሪፖርቱን ለየሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበበት ወቅት***

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወይዘሮ እጸገነት መንግሥቱ በበኩላቸው፣ ምንም እንኳን የዲሞክራሲ ምኅዳሩ እንዲሰፋ ቢደረግም፣ ኹሉም ድርጅት ጤነኛ አስተሳሰብ ይዞ ስለማይመጣ በምዝገባ ወቅት የማጣራት እና ጥብቅ ጥንቃቄ የማድረግ ሥራ በትኩረት ሊከናወን እንደሚገባ ማሳሰባቸው ተሰምቷል።

በሌላ በኩል፣ ፈቃድ ለማግኘት ካመለከቱ 485 ድርጅቶች መካከል መስፈርቱን ባለማሟላታቸው እና አስፈላጊውን ክትትል ባለማድረጋቸው ጥያቄያቸው ተቋርጦ እንዲሰረዝ የተደረጉ መኖራቸው ሲጠቀስ፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ 319 ድርጅቶች በምዝገባ ሂደት ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል። የተመዘገቡት ድርጅቶች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን በማስመልከት ከቋሚ ኮሚቴው ለቀረበው ጥያቄ፣ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሳምሶን ቢራቱ ምላሽ ሰጥተዋል። ማንኛውም ዜጋ የመደራጀት እና የመመዝገብ መብት እንዳለው በሕገ-መንግሥቱም ሆነ በባለሥልጣኑ ዐዋጅ የተፈቀደ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ግን ከአገር ደኅንነት አኳያ በጥልቀት እንደሚታዩ አብራርተዋል። በተለይም የውጭ አገር ድርጅቶች በሚሆኑበት ወቅት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ጋር በጋራ በመሆን የኋላ ታሪካቸውን የማጥናት ሥራ እንደሚከናወን ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚያገኙት ሀብት ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል ተብሏል። ይኽ ቁጥጥርም ድርጅቶቹ በየዓመቱ በሚያቀርቡት ሪፖርት አማካኝነት ከሀብታቸው አጠቃቀም አንጻር እየታየ የሚገመገም እና ተገቢው ግብረ-መልስ የሚሰጥበት መሆኑን ፋሲካ ሞላ ጨምረው አስረድተዋል።

በዚኹ የባለሥልጣኑ ሪፖርት ላይ የተጠቀሰው ሌላው አንኳር ጉዳይ፣ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በቀጣዩ ምርጫ ይኖራቸዋል ከተባለው ሚና አኳያ ነበር።

ከምክር ቤቱ እንደተገኘው መረጃ ከሆነም፣ በሰባተኛው አገራዊ ምርጫ የሚሳተፉ ሀገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ነጻነታቸው እና ገለልተኝነታቸው ላይ ጥያቄ ሊነሳባቸው እንደማይገባ ቋሚ ኮሚቴ ማሳሰቡ ተጠቅሷል።



***የኢፌድሪ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን አመራሮች እና  የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት***

ቋሚ ኮሚቴው፣ ድርጅቶቹ ለተደራጁለት አላማ ብቻ ሀብታቸውን መዋላቸውን ማረጋገጥ እና ጠንካራ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ገልጿል። በአኹኑ ወቅትም 212 ሀገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምርጫ ሂደት ላይ ለመሳተፍ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፈቃድ ማግኘታቸው የጠቀሱት የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ምክትል ዳይሬክተሩ ፋሲካ ሞላ መሆናቸው ተዘግቧል፤ ይኽም ከስድስተኛው አገራዊ ምርጫ ጋር ሲነጻጸር የተነቃቃ እንቅስቃሴ መኖሩን እንደሚያሳይ ተመላክቷል። ቋሚ ኮሚቴው በምርጫ ማስተማር እና በታዛቢነት ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ ድርጅቶች ገለልተኝነት እጅግ ወሳኝ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቷልም ተብሏል። ድርጅቶቹ ምርጫውን በገለልተኝነት እንዲደግፉ እና አላስፈላጊ ተግባራት ውስጥ እንዳይገቡ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ክትትል እንዲያደርግ አሳስቧል።

ከዚኽ በላይ አጠር አድርገን ካየናቸው የሦሥቱ መንግሥታት እና የሲቪል ማኅበረሰቡ ያዝ-ለቀቅ መስተጋብር አንጻር፣ አኹን ያለው የማኅበራቱ እንቅስቃሴ በንጽጽር ደህና ይመስላል የሚሉ ሙግቶችም ይደመጣሉ። ያም ቢሆን፣ ከቀጣዩ ምርጫ 2018 አኳያ፣ አኹን ያሉት የሲቪል ማኅበራት ምን አገራዊ ኃላፊነቶች አሉባቸው የሚለውን አስቀድመን በመጥቀስ፣ ከመንግሥትም ሆነ ይመለከታቸዋል ከሚባሉ መንግሥታዊ ተቋማት፣ ሲቪል ማኅበረሰቡን ለማጠናከር ምን ጉዳዮች በቅጡ መታየት እንዳለባቸው አጠር ያሉ ምክረ-ሐሳባዊ ነጥቦችን እናስከትላለን።

## 7.8. ምርጫ 2018 እና የሲቪል ማኅበረሰቡ ሚና

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በቀጣዩ ምርጫ ሂደት ውስጥ ከምርጫ አሥፈጻሚው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከመንግስት እና ከተገዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቀጥሎ ሦሥተኛው ወሳኝ ምሰሶ ናቸው። እናም፣ በ2018 ምርጫ የሚከተሉት ሦሥት ዋና ዋና ሚናዎች ይጠበቁባቸዋል ብለን እናምናለን።

### ሀ፦ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢነት

እንደሚታወቀው ይኸ የሲቪል ማኅበረሰቡ ቀዳሚ ተግባር ነው። ይኸንን ግብር ይከወኑ ዘንድም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 114 እና 117፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(7) እና አንቀጽ 8(1) ተከትሎ በወጣው የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች የዕውቅና አሰጣጥ፣ የአሠራር ሥርዓት እና የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 5/2012 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፤ በ7ኛው አጠቃላይ ምርጫ የሚሳተፉ 45 የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶችን መዝግቦ ዕውቅና ሰጥቷል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሰባተኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ያላቸው ተሳትፎ መጨመሩ ለዲሞክራሲ ምኅዳሩ ግንባታ አዎንታዊ እርምጃ ቢሆንም፣ ድርጅቶቹ ከየትኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይኖርባቸዋል። ቋሚ ኮሚቴው እንዳሳሰበው፣ ድርጅቶቹ በምርጫ ታዛቢነትም ሆነ በማስተማር ተግባር ላይ ሲሰማሩ "ጤነኛ አስተሳሰብ" ይዘው መቅረባቸውን እና የገለልተኝነት ጥያቄ እንዳይነሳባቸው በገለልተኛ አካል የሚመራ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት የራስ በራስ ቁጥጥር የሚያደርጉበትን መዋቅር መዘርጋት ይኖርባቸዋል ማለት እንሻለን።

ከዚኽ ባለፈም፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ በምርጫ ጣቢያዎች (በተለይም ከከተማ ወጣ ባሉት ጣቢያዎች) በመገኘት የዜጎች ድምፅ አሰጣጥ እና ድምጽ ቆጠራው በሕግ እና በሥርዓት መከናወኑን በሚገባ መከታተል ይኖርባቸዋል። ከዚያም፣ የታዘቡትን ግድፈትም ሆነ ጥንካሬ ለመራጩ ሕዝብ እና ለዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ይፋ በማድረግ የምርጫውን ቅቡልነት መወሰኛ መስፈርት ለማድረግ ሊተጉም ይገባል።

## ለ፦ የመራጮች ትምህርት

ለቀጣዩ አጠቃላይ ብሔራዊ ምርጫ የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ 143 የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶችን መዝግቦ ዕውቅና ሰጥቷል። ከዚኽ አኳያ ስንመለከተውም፣ በእርግጥም መራጮች በቂ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ አካታች፣ ተሳታፊ እና ግልጽ የሆነ ትምህርት በመስጠት ረገድ የሲቪክ ማኅበረሰብ ሚና የማይተካ ነው።

እነኽ እውቅና የተሰጣቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምርጫውን አስመልክቶ የሚሰጧቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች፣ ኹሉንም መራጭ የማኅበረሰብ ክፍል ተደራሽ ሊያደርጉ ከመገባቱ በተጨማሪ፣ በሚችሉት ልክ በኹሉም ቋንቋዎች እና በተለይም በሴቶች እና በአካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚኖርባቸው ማስታወስ ያሻል። ዜጎች ስለ መብታቸው እና ስለ ድምፅ አሰጣጥ ሂደት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ በዋናነት የሚጠበቀው ከሲቪል ማኅበረሰቡ መሆኑ አሌ

አይባልም። በዚኽም ዜጎች በምርጫው በንቃት እንዲሳተፉ ከማነቃቃት አልፎ፣ በምርጫው ወቅት የሚሰራጩ የሐሰት ወሬዎችን በማረም ዜጎች በእውነት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጡ መርዳት ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን።

### ሐ፦ መድረኮችን መፍጠር እና ግጭቶችን መከላከል

ብዙ እንደተጻፈውም፣ በእኛም የፖለቲካ ተላምዶ እንደተመለከትነው፣ ምርጫ በተፈጥሮው ውድድር ያለበት በመሆኑ ውጥረቶችን ሊያጭር ይችላል። ከዚኽ አንጻርም፣ በቅድመ-ምርጫውም ሆነ በድህረ-ምርጫው ወቅት፣ ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ምልክቶችን በመለየት ከመንግሥት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችም ይሰሩ ዘንድ ዜግነታዊ ኀላፊነታቸውን መወጣት እንደሚኖርባቸው ማታወስ እንሻለን። ከዚኹ ጋር በተያያዘም፣ በተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርተዎች መካከል ሰላማዊ የሐሳብ ፍሰት እንዲኖር፣ ቀኑ ሳይገፋ የውይይት መድረኮችን ያመቻቹ ዘንድም ብሪጅ አበክራ ትጠይቃለች።

## 7.9. የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች

ሲቪል ማኅበረሰቡ እነዚኽን ሚናዎች በቀጣዩ የ2018 ምርጫ ላይም ሆነ ከዚያ በኋላ በሚኖራቸው እንቅስቃሴዎች፣ ለመወጣት ይቻላቸው ዘንድ፣ ብሪጅ ቀጣዮቹን አጠር ያሉ ምክረ-ሐሳቦች ለሚመለከታቸው የመንግሥት መዋቅሮች ማቅረብ ትሻለች።

### ሀ፦የሀብት አቅርቦትን መጨመር

በአሜሪካ መንግስት ይደገፍ የነበረው የአሜሪካ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ ለሲቪል ማኅበረሰቡ ይሰጥ የነበረውን ድጋፍ ካቋረጠ ዓመት ማለፉ ይታወቃል። ሲቪል ማኅበረሰቡም በነበረበት የፋይናንስ ዕጥረት ላይ ይኽ መከሰቱ፣ ሰፊ ተቋማዊ መዳከምን አምጥቷል። እናም፣ ይኽን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የፌደራሉ መንግሥትም ሆነ ይመለከተናል የሚሉ መንግስታዊ የልማት ተቋማት፣ ለሀገር በቀል ድርጅቶቹ (በተለይም በቅርቡ ለተቋቋሙት እና አዲስ ለሚቋቋሙት) የተለያዩ ሀገር-በቀል ድጋፎችን የሚያገኙበትን የሕግ ማዕቀፍ ሊያዘጋጁ(ለማሳያም፣ ከገቢ ግብርም ሆነ ከሌሎች የግብር ዓይነቶች የሚኖሩ ማበረታቻዎችን)፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና ዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ምንጮችን የሚያገኙበትን ዕድል ሊያመቻቹ ይገባል እንላለን። ከዚኽ ባለፈም፣ በውጭ ዕርዳታ ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ፣ የአገር ውስጥ በጎ አድራጎት ባህልን ማሳደግ እና ድርጅቶቹ የአገር ውስጥ የገንዘብ ድጋፎችን የሚያገኙበትን የሕግ ሥርዓት መዘርጋትም መዘንጋት እንደሌለበት ማስታወስ ያስፈልገን ይሆናል።

### ለ፦ የአገር ደኅንነት ፍተሻ እና የመመዝገብ መብት መጣጣም

ዜጎች የመደራጀት ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉ፣ የምዝገባ ሂደቱ ከብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ጋር ተቀናጅቶ መከናወኑ ለአገር ደኅንነት ዋስትና መሆኑ አያከራክርም። ሆኖም፣ ይኽ የደኅንነት ፍተሻ ሂደት ለሲቪክ ማኅበራት ምዝገባ መዘግየት፣ ለቁጥር ማነስ ወይም ለቢሮክራሲያዊ እንቅፋት እንደ ሰበብ ሊቀርብ አይገባም።

ከዚኽ አኳያም፣ የደኅንነት ሥጋትን ከመቀነስ ጎን ለጎን፣ ተቋማዊ ግልጽነትን ለማረጋገጥ እና አላስፈላጊ መስተጓጎልን ለማስወገድ ሊወሰዱ ይገባቸዋል ብላ ብሪጅ ከምታምንባቸው አሥተዳደራዊ እርምጃዎች መካከል ቢያንስ ሦሥቱን መጥቀስ ትሻለች፤ ቀዳሚው የግልጽ መመሪያ መኖር አስፈላጊነት ሲሆን፤ የደኅንነት ምርመራው መመዘኛዎች በግልጽ ተለይተው የሚታወቁበት እና ከሕግ አግባብ ውጭ በሆኑ ግላዊ ውሳኔዎች የማይመሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

ሌላይኛው፣ እንደተባለው የምርመራ ሂደቱ በዘመናዊ የዲጂታል ሥርዓት የታገዘ እና የተቀላጠፈ እንዲሆን ሲደረግ፣ በሕግ የተቀመጠውን የምዝገባ የጊዜ ገደብ የሚያከብር መሆን ይኖርበታል። በመጨረሻም፣ የደኅንነት ፍተሻው በዜጎች መሠረታዊ መብት ላይ የማይታይ ቢሮክራሲያዊ አልያም ፖለቲካዊ መሻትን የተንተራሰ ቀይ መስመር ከመሆን ወጥቶ፣ ሕጋዊ ድርጅቶች ያለ አንዳች ቢሮክራሲያዊ ማነቆ ወደ ሥራ የሚገቡበትን ኹኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል እንላለን።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

"እንደራሴ" የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው "እንደ" እና "ራሴ" ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። "እንደ"፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ "ራሴ"፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ "እንደ እኔ" ወይም "እኔን ሆኖ" ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ "እንደራሴ" የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው "ቢትወደድ-እንደራሴ" ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ 'ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ'ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን "እንደራሴ" ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ'ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች "የሕዝብ እንደራሴዎች" መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ "ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ"፣ "ምስለ-ሕዝብ" አልያም "የሕዝቡ ተወካይ" የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ "ተወካይ" (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም "እንደራሴ" የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ "እንደራሴ" ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት 'የራስን ዕድል በራስ የመወሰን' ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው 'ራስ'፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ "እንደራሴ" ውስጥ ያለውን 'ራሴ'ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ "እንደራሴ" ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን 'ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ' ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ"እንደራሴ" ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu'aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

---

**ከራስ ውርድ፦**

"በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።"

# እንደራሴ

አንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 99 808 5013

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, O ce No. 5, Addis Ababa.